ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ.ም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

FDRE Office of the Federal Auditor General

2011 ዓ.ም

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ራዕይ

በ2017 ዓ.ም በአፍሪካ ካሉት ምርጥ የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤቶች አንዱ መሆን፤

ተልዕኮ

የሙያ ነፃነትን መሰረት ያደረገ ሰፊ ሽፋንና ጥራት ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ወቅታዊ የኦዲት አገልግሎት በመስጠት መልካም አስተዳደር ለማስፈን እና የመንግስትን የአፈጻጸም ብቃት ለማሳደግ እገዛ ማድረግ፤

እሴቶች

የቡድን ስራ= Team work
ተጠያቂነት= Accontablity
ተአማኒነት= Reliablity
ሀቀኝነት= Integrity
ቁርጠኝነት= Commitment

ምስጋና

የሽፋን ገጽ ፎቶ በመስጠት ለተባበረን ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምስጋና እናቀርባለን።

ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ.ም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተዘጋጀ
2011 ዓ.ም

ማውጫ

ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ.ም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት..........1

የ2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን..........3

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ..........3

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች..........4

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች..........5

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት..........5

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ..........5

የገቢ ሂሣብ..........7

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ..........7

መሰበሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ ሂሳብ..........8

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ 9

ተሰብስቦ በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ..........10

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ..........10

የወጪ ሂሣብ..........11

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ..........11

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች..........12

በብልጫ የተከፈለ ወጪ..........13

የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች..........14

ንብረቱ ገቢ ስለመሆኑ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ..........15

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ..........16

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ..........17

የማማከር ፈቃድ ሣይኖር ያለአግባብ ተረጋግጦ የተፈጸመ
የግንባታ ክፍያ..17
በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ...18
የተከፋይ ሂሣብ..19
በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ...19
የበጀት አጠቃቀም...20
ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ 20
የንብረት አስተዳደር..20
የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ...22
የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ........24
የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ.........................24

የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ...26

የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ስርዓት አፈጻጸም ውጤታማነት
በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት...26
የወጪ ንግድ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት..........................28
የለሁሉ ኮንትራት አሰጣጥ እና አፈፃፀምን በተመለከተ
የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት..30
የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓትን
የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ወይም ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት
ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት................................33
የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት...................35
የ11 አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት
አስተዳደር ስርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት....................36
የእንቦጭ አረም በሀይቆችና ወንዞች ላይ ያስከተለውን
ስጋትና ችግር ለመፍታት የተዘረጋውን ስርዓት ውጤታማነት
በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት...38
ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር
አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት...39
የመንገድና ድልድይ ጥገና አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት..............41
የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት
("የምድብ 'ሐ' ሕንፃ") በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት..................................42
በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት.........................43

የልዩ ኦዲት ስራዎች..44

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ

እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ.......................................44

የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት..............................46

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ..................................46
ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ..46
የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ..47
የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ..48
የ2010 በጀት ዓመትና 2011 በጀት ዓመት የዘጠኝ
ወር የበጀት አጠቃቀም..49
መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች.....................................49
የ2011/2012 ኦዲት ዓመት ዕቅድ..50

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች

የተከናወነ ኦዲት...51

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሣብ መግለጫዎች
ላይ የተሰጠ የኦዲት አስተያየት...51
የኮርፖሬሽኑ የኦዲት ዕቅድ ክንውን...52
የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ አንቅስቃሴ..52

ማጠቃለያ..53

አባሪ 1፡- በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እና ባለፉት ተከታታይ ሁለት ኦዲቶች ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው እና አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች...56

አባሪ 2- ሂሣባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች..........59

አባሪ 3- ልዩ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶችና የኦዲት አርዕስቶች.........................62

ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ.ም

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

- **የተከበሩ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፤**
- **የተከበሩ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ም/አፈ ጉባዔ፤**
- **የተከበራችሁ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤**
- **ክቡራትና ክቡራን፤**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15 እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም አማካይነት የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፣ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወኑ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውንና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic Services III) ተከታታይ እና ማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት እና የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ በተመለከተ የተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፡፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሂሳብና በመንግስትና የልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡

3. የ2010/11 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 11 መ/ቤቶችና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 49 መ/ቤቶች እንዲሁም የ23 አዳዲስና የ5 ክዋኔ ኦዲት የክትትል ኦዲት ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹም ቅጅ 2 ጥራዞች/ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት እና አጠቃላይ ዘገባ/ እና ሌሎች የተጠቀሱት ሪፖርቶች በሶፍት ኮፒ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም ሌላ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት

ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የመንግሥት የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ ኦዲቱ የተከናወነውም በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የ2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

7. የ2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ መሠረት ያደረገው የመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1-15 እና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 (በአዋጅ 970/2008 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀፅ 2 ነው፡፡ በየዓመቱ የኦዲት ሥራው የሚጀመረው በመጋቢት ወር ሆኖ የሚጠናቀቀው በቀጣዩ በጀት ዓመት ጥር 30 ላይ ይሆናል፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 182 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 176 መ/ቤቶችንና 46 ቅ/ጽ/ቤቶቻቸውን እና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት በመ/ቤታችን አማካይነት፣ የተቀሩትን ስድስቱን ደግሞ በሂሳብ ምርመራ አገልገሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ ተደርሶበት የነበረውን የኦዲት ሽፋን 100% ለማስቀጠል የታቀደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 176 መ/ቤቶች መካከል የአንድ ዩኒቨርሲቲ ኦዲት በወቅታዊ ፀጥታ ችግር በመቋረጡና አንድ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ሂሰቡን ዘግቶ ማስመርመር ባለመቻሉ የ174 መ/ቤቶችና 46 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት የተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ የፌዴራሉ መንግሥት የ2010 በጀት ዓመት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትም በመከናወኑ በአጠቃላይ

የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸም 98.87% ሆኗል። በመሆኑም ከመ/ቤታችን ቁጥጥር ውጭ በሆነው ምክንያት የ2010 የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሽፋን ቀደም ባሉት ዓመታት ከነበረበት 100% ወደ 98.87% ዝቅ ሊል ችሏል።

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ174 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን የባለበጀት መ/ቤቶቹ ሪፖርቶችም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2008 እና 2009 ካሉት በጀት ዓመታት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት አስተያየቶች ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል።

መግለጫ	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2008	2009	2010
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	27	25	25
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	73	87	89
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	5	8	11
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	53	53	49
የኦዲት ስራው የተቋረጠ			1
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ	-	-	1
ድምር	158	173	176

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ በ2010 ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከህግና ከተዘረጋው አሠራር ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፣ የም/ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ የሚገቡ አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርቧል።

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 810,060.38፣ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 123,599.00 እና በጅግጂጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 27,173.28 በድምሩ ብር 960,832.66 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል።

12. በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ2 የገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቆጠራው ከመዝገብ ጋር ሲነፃፀር በብር 102,532.99 በማነስ ልዩነት ታይቷል። እንዲሁም በ14 መ/ቤቶችና በ14 ቅ/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል።

13. የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ በጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት፣ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ፣ በማነስ የታየውም ልዩነት ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና የታዩት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል።

የውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ

14. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ129 መ/ቤቶችና በ10 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,252,562,207.37

በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል።

15. በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ውስጥ የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 608,731,337.69፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 441,828,292.09፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 322,520,418.09፣ የቀድሞው ውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 282,965,014.42፣ የቀድሞው መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 256,674,976.65፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 250,218,048.94፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 232,084,916.72፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 169,647,495.93፣ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 160,457,088.68፣ ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 153,255,211.99፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 108,079,052.31፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 114,611,493.86፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 111,362,647.02 እንዲሁም አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 102,777,501.69 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

16. በወቅቱ ያልተወራረደው የተሰብሳቢ ሂሳብ በዕድሜ ቆይታው ሲተነተን ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 763,279,769.15፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 2,356,252,611.41፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 524,990,497.56 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 168,604,776.56 ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ብር 439,424,322.50 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው።

17. ከላይ በፓራግራፍ 14 ከተጠቀሰው ተሰብሳቢ ሂሳብ በተጨማሪ በ9 መ/ቤቶች እና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,298,391,518.67 ከመቼ ጀምሮ በተሰብሳቢነት እንደተመዘገበና ከማን እንደሚሰበሰብ በቂ ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 1,203,900,478.44፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 33,064,845.86 እና የቀድሞ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ብር 23,412,458.30 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

18. በሌላ በኩል በ10 መ/ቤቶችና 7 ቅርንጫፎች ከተለመደውና ከሚጠበቀው የተሰብሳቢ የሂሳብ ሚዛን በተቃራኒ በብር 52,054,783.31 ክሬዲት የሚታይ በመሆኑ በመ/ቤቶቹ ሊኖር የሚገባውን ተሰብሳቢ ሂሳብ በዚሁ መጠን እንዲያንስ ማድረጉ።

19. በተጨማሪም በአንድ መ/ቤት አላግባብ ከመዝገብ የተሠረዘ ብር

9,712,330.24 እና በ3 መ/ቤቶች ደግሞ የተቀፅላ ሌጀር የሌለ በመሆኑ ከማንና መቼ እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ብር 361,743,928.36 ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል።

20. በመሆኑም መ/ቤቶች ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቦቹን ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተከታትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ተጣርቶ ትክክለኛነቱ በማስረጃ እንዲረጋገጥና እንዲሰበሰብ ወይም እንዲወራረድ፣ ትክክለኛ ሚዛን የማያሳየውም ተጣርቶ እንዲስተካከል እና አላግባብ ከመዝገብ የተሠረዘው ወደ ቦታው እንዲመለስና እንደገና እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል።

የገቢ ሂሣብ

21. የመንግሥት ገቢ በወጡት ሕጎች መሠረት በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ

22. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቀድሞው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብር 302,835,172.76፣ በሌሎች በ59 መ/ቤቶችና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 54,615,686.58 በድምሩ ብር 357,450,859.34 ሣይሰበሰብ ተገኝቷል።

23. በደንቡ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል በቀድሞው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ብር 129,320,116.87፣ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 42,103,121.15፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,515,511.90 እና የምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 25,685,575.29 ሲሆን ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 12,625,775.80 እና የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 10,666,140.00፣ የፌዴራል የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 5,723,497.08 እና የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,754,022.70 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

24. የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ የመጫኛ/ማራገፊያ፣ የባህር ትራንስፖርት፣ የየብስ ትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ወጪ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ እንዲሁም ማስረጃ ባለመቅረቡ፣ በግብይት ዋጋ (FOB) ላይ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ (marine insurane) ወጪ ባለመደመሩ፣ እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ ባለመመደባቸው፣ የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት የትራንስፖርት ወጪ በአግባቡ ባለመካተቱ፣ በትክክለኛ የቀረጥና ታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ፣ ዕቃው በዲክላራሲዮን ላይ በተመዘገበበት ቀን በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት ባለመሰላቱ፣ ተሽከርካሪዎች ምንም አይነት አገልግሎት ካልሠጡ የእርጅና ተቀናሽ ሳይደረግ በአዲስ ዋጋ መሠረት ቀረጥና ታክስ መሰራት ሲገባው የእርጅና ቅናሽ በመካተቱ፣ የቀረጥ ነጻ ማስረጃ ሳይቀርብለት ከቀረጥና ታክስ ነፃ በመግባቱ፣ የዕቃው ዋጋ በዕቃዎች አካላዊ ፍተሻ ሪፖርት መሰረት ባለመሰራቱ፣ በአየር ማጓጓዣ ክፍያ አንድ ሦስተኛው እና የማራገፊያ የመንከባከቢያ ወጪ ቀጥታ ተወስዶ ባለመሰራቱ፣ ለረዥም ዓመታት በፖስታ አገልግሎት ድርጅት ስም በተሰብሳቢ ተይዞ ለቅ/ፅ/ቤቱ ገቢ ያልተደረገ ቀረጥና ታክስ መኖሩ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

25. በመሆኑም መ/ቤቶቹ ለወደፊቱ የመንግሥትን ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸውና በተለያዩ ምክንያቶች እስከዚያን ጊዜ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ ሂሳብ

26. በፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሠረት አቅራቢው ሣይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግሥት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10% ሣይበልጥ የጉዳት ካሣ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያመለክታል። በዚህ መሠረት መ/ቤቶች በውሉ መሠረት ባልፈጸሙት አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ላይ በመመሪያው መሠረት ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑ ሲጣራ በ15 መ/ቤቶች

ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች ጋር በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልሰበሰቡት ብር 53,033,612.64 የጉዳት ካሣ ወይም ቅጣት ተገኝቷል። በተጨማሪም በተፈረመው የውል ስምምነት መሠረት በ3 መ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ብር 3,634,488.76 የሱቅና ሌሎች የኪራይ ገቢና ቅጣት እና በገቡት የትምህርት ውል መሠረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ የትምህርት ክፍያ ብር 379,831.22 እና የአሜሪካን ዶላር 156,536.17 ተገኝቷል።

27. የጉዳት ካሣውን ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,773,046.02፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,944,004.78፣ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,301,977.07 እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,422,029.93 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

28. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በመንግሥት መመሪያና በገቡት ውል መሠረት እስከ አሁን ያልተሰበሰበውን የጉዳት ካሣና ሌሎች ገቢዎች እንዲሰበስቡና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሠረት እንዲፈጽሙ አሳስበናል።

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

29. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቀድሞው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አስራ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ሦስት መ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፣ ወለድ፣ ቅጣት እና ዱቤ ሽያጭ መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 7,670,055,993.73 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ታውቋል።

30. ውዝፍ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በቀድሞው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,452,745,400.00፣ የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 991,128,073.20፣ የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 549,978,782.00 እና የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት ብር 484,094,194.69 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

31. በሌላ በኩል በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በዋናው መ/ቤት ውሳኔ የተሰጠ ቢሆንም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል ውሳኔው ባለመታወቁ ወይም ባለመገለጹ ያልተሰበሰበ ብር 1,312,069,929.97 ውዝፍ የግብር፣ ቀረጥና

ታክስ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

32. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት የሚያከናውናቸውን ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና መሠረተ ልማት ለመዘርጋት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ተሰብስቦ በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

33. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ10 መ/ቤቶች ብር 157,466,831.46 የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳያካትቱ ተገኝቷል፡፡

34. የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አሁንም አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ ይህ አሰራር በገቢ ሂሳብ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ለምዝበራ በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ መ/ቤቶቹ የሚያዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎችና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

35. በሌላ በኩል በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ባለበጀት መ/ቤቶች ያልተጠቀሙበትን በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ማድረግ የሚኖርባቸው ቢሆንም በቀድሞ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና በ4 ዩኒቨርሲቲዎች ብር 84,426,812.27 ፈሰስ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

36. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውንም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ እንዲመዘግቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸው በማካተት ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያደርጉና እንዲጠቀሙበት በሕግ ያልተፈቀደላቸውን ገቢ ሂሳብም ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

37. የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገቢዎችና

ጉምሩክ ባለስልጣን በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 838,005,022.16 እንዲሁም በ7 ሌሎች መ/ቤቶች የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 12,533,320.71 አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በሌላም በኩል በናሙና ከታዩት ፋይሎች ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያላሳወቁ 40 ግብር ከፋዮች እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 34 ግብር ከፋዮች የተገኙ ሲሆን የሚፈለግባቸው ግብር ሂሳብ ምን ያህል እንደሆነና ግብሩንም ስለመክፈላቸው ወይም ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

38. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች ዝርዝር በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ግብር ከፋዮች የሚፈለግባቸውን ግብር በሙሉ በወቅቱ አሳውቀው እንዲከፍሉ ተገቢውና ጥብቅ ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሣብ

39. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውና መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

40. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ63 መ/ቤቶች ብር 1,475,867,250.28 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

41. 4የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 842,885,505.51፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 356,715,318.54፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 129,587,507.28፣ ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 29,381,996.90፣ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ብር 18,952,906.73፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,663,770.37፣ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 9,329,585.59፣ የብሔራዊ የቆላ ዝንብ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ብር 8,805,060.25 እና ውጭ ጉዳዩ ሚኒስቴር ብር 6,354,207.54 ዋና

ዋናዎቹ ናቸው፡፡

42. ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ የተወዳዳሪዎች የንግድ ስራ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ስርተፊኬት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ የአገልግሎት ሰጪውንና የአገልግሎት ተቀባይን የውል ስምምነት የሚያሳይ ውል ሳይኖር ወጪው እንዲከፈል በተጠየቀ ደብዳቤ መሰረትብቻ የተከፈለ፤በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ በውጪ ሀገር ለተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተከፈለ ክፍያ ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የተሳታፊዎች ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ፤ የቀረቡት ህጋዊ ያልሆኑ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለ መድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው፡፡

43. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ወጪውን የሚደግፉ ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፤ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

44. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ77 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 145,676,300.91 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

45. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- ትምህርት ሚኒስቴር ብር 73,982,403.47፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 10,569,744.81፣ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,960,196.57፣ ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ብር 7,671,634.60፣ የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,507,155.91፣ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,196,212.00፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር

6,001,671.53፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,317,438.53 እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,997,077.17 ሲሆኑ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ መፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል መክፈል፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት በሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ መክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

46. በሌላ በኩል የስራው ባህሪ ቋሚነት ወይም ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በቀድሞው የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር በ8 መ/ቤቶች የብር 13,904,355.05 የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በሌሎች 14 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና 15 መ/ቤቶች ተመራማሪዎች ጥናት ላቀረቡበት፣ ለፈተና ግምገማ፣ የማስተርስና ፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ፈተና የፈተኑበትና የገመገሙበት ክፍያ፣ ለመመረቂያ ጽሁፍ ማማከር ሥራዎች እና ሌሎች ምክንያቶችን በመጥቀስ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 41,703,125.15 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

47. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆን፤ የክፍያ ስርዓት ለሌላቸው ሥርዓቱን በመዘርጋትና በማስፈቀድ ለወደፊቱ ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

በብልጫ የተከፈለ ወጪ

48. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ የተከናወኑ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች ለግንባታና ለተለያዩ ሌሎች ግዢዎች ብር 3,266,061.85 እና በ55 መ/ቤቶች እና 1 ቅርንጫፍ ደግሞ ለደመወዝ፣ ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 28,875,144.17 በጠቅላላው ብር 32,141,206.02 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

49. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ያለበቂ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ ከተገባው ውል ውጭ በመክፈል፣ ለደመወዝ ከሚገባው በላይና ከውሉ አበል ተመን በላይ በመክፈል፤ እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፣ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈሉ ይገኙበታል።

50. ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ ህግን የተከተለ ካለመሆኑም በላይ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግና ለሙስናም በር የሚከፍት አሠራር ነው። በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆንና አስፈላጊውም አስተዳደራዊ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል።

የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች

51. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ100 መ/ቤቶችና 8 ቅ/ጽ/ቤቶች በጨረታ መፈጸም ሲገባ ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በብር 802,199,221.84 ግዥ መፈጸሙ፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የብር 5,937,639.38 ግዢ መከናወኑ፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የብር 78,267,524.87 ግዥ መፈጸሙ፣ በዋጋ ማወዳደሪያ መገዛት ሲገባው የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የብር 18,393,839.63 ግዥ መፈጸሙ እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ የብር 52,024,352.94 በድምሩ ብር 956,822,601.96 የመንግሥት የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

52. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፤ ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 556,832,185.29፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 96,974,563.35፣ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 43,360,623.00፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,697,650.65፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 17,927,784.00፣ ወራቤ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,574,142.14፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,663,136.22፣ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ብር 15,415,976.04 እና ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,956,353.16 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

53. በሌላ በኩል በ11 መ/ቤቶች የተገዙት ዕቃዎች በናሙናው መሠረት ገቢ

ለመሆናቸው ሣይጣራና የተጠየቀው አገልግሎት ስለመስጠቱ በባለሙያ ወይም በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የብር 21,628,420.99 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል።

54. የግዥ መመሪያን ሳይከተሉ ግዥ መፈጸም የህግ ጥሰት ከመሆኑም በላይ መንግሥት ተወዳዳሪ ዋጋ እንዳያገኝ ለምዝበራና ለጥራት መጓደል የሚያጋልጥ በመሆኑ የመንግሥት ግዥ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

ንብረቱ ገቢ ስለመሆኑ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

55. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ20 መ/ቤቶች በብር 2,006,431,091.87 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል። በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶች ብር 1,361,059,364.44 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀርብ የቀረጥ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል።

56. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳያቀርቡ ሂሳቡን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,928,982,791.60፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,020,535.36፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,442,455.35 እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ብር 10,151,406.77 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያላቀረቡት ደግሞ የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,311,908,803.11፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 23,969,464.20 እና የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 22,173,426.52 ናቸው።

57. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚገዛው ማንኛውም ንብረት የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶለት ለመ/ቤቱ ገቢ ተደርጎ ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግሥትና የህዝብ ንብረትና ገንዘብ በቀላሉ ለብክነትና ለሥርቆት ሊዳረግ ይችላል።

58. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም

የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡ የተከፈለበት ንብረት በዕቃ ገቢ ደረሰኝ ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ ካልሆነም ከሚመለከታው አካል ጋር ተነጋግረው አሠራር እንዲዘረጋለት እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

59. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ10 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የኮንትራት አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 186,009,704.35 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

60. የቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 116,821,986.39፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 41,573,161.15፣ የቀድሞው መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 15,437,979.87 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 6,078,078.54 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

61. በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለተቋራጮች የሰጠው ቅድሚያ ክፍያ ብር 5,106,668.90 እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር ለተቋራጮች ከሰጠው የሲሚንቶ ብድር ብር 53,130,865.05 በድምሩ ብር 58,237,533.95 ከቅድሚያ ክፍያና ሲሚንቶ ብድር ያልሰበሰቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሣብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ የግንባታ ክፍያዎችም በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት ከእያንዳንዱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተቀንሶ ለመንግሥት ተመላሽ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በብድር የተሰጠ ሂሳብም ከማን ምን እንደሚፈለግ ተይዞ መሰብሰብ አለበት፡፡

63. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብና ተቀናሽ ያልተደረገው ቅድሚያ ክፍያና የሲሚንቶ ብድር ተጣርቶ ለመንግስት ተመላሽ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

64. በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸውና ትክክለኛ ወጪ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ27 መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ብር 413,280,996.45 ማስረጃ የሌለው በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

65. ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች መካከል የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ብር 134,472,633.18፣ የቀድሞው መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 95,100,095.07፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 53,772,357.80፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 50,633,757.50፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 41,937,315.62 እና ጤና ሚኒስቴር ብር 13,456,488.42 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

66. ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ የመንግሥትን ገንዘብ ወጪ ማድረግ ህግና አሠራር መጣስ ከመሆኑም በላይ የህዝብንና የመንግሥትን ገንዘብ ለጥፋትና ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ ሆኖ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የማማከር ፈቃድ ሣይኖር ያለአግባብ ተረጋግጦ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ

67. ማንኛውም ግንባታ ሲከናወን ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ የማማከር አገልገሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ ድርጅት ሲረጋገጥ ብቻ ክፍያዎች ሊፈጸሙ ይገባል፡፡ ሆኖም የግንባታ ፕሮጀክቶችን ሥራ እንዲከታተሉ በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ እንደአንድ የስራ ክፍል የተቋቋሙ ነገር ግን የማማከር ፈቃድ በሌላቸው የግንባታ ጽ/ቤቶች የክፍያ ሠርቲፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በማከናወን በ4 ዩኒቨርሲቲዎች ብር 114,959,683.05 ወጪ ተደርጓል፡፡ በአንድ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በአማካሪ ባልጸደቀ የክፍያ ምስክር ወረቀት ብር 36,238,839.25 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ይህ አሠራር ህጋዊ ባለመሆኑ እንዲቋረጥ ከ2007 ጀምሮ ብናሳስብም የተወሰኑ ተቋማት እርምጃ ሳይወስዱ አሁንም ተግባሩን

ገፍተውበታል።

68. በሌላም በኩል የትምህርት ሚኒስቴር የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ሣይፈረም ብር 18,629,844.49፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህግ የሚፈቅደው ከመጀመሪያው ውል እስከ 30% ሆኖ ሳለ ከተፈቀደው በላይ ብር 1,270,586.85 ውል የገባ ሲሆን አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ደግሞ ለአገልግሎትና ዕቃ ግዥ ከመጀመሪያው ውል እስከ 25% ብቻ ተጨማሪ ግዢ መግዛት እንደሚቻል የተፈቀደ ቢሆንም ከተፈቀደው በላይ ብር 9,001,699.77 ውል ተገብቶ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

69. ግንባታዎች በተገቢው ጥራትና በዲዛይኑ መሠረት ስለመሠራታቸው በህግ አግባብ ዕውቅና በተሰጠው ገለልተኛ አካል ማረጋገጫ ተሰጥቶ ክፍያ ካልተፈጸመ የተከናወነውን ግንባታ በተመለከተ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ስለማያስችል መ/ቤቶቹ እየተከተሉት ያለው አሠራር በፍጥነት እንዲቋረጥና ለግንባታዎች ተገቢው ዕውቅና ያለው አማካሪ ድርጅት እንዲቀጠር ቀደም ባሉት ዓመታትም በተደጋጋሚ ብናሳስብም አሠራሩን ለማረም ፈቃደኛ ያልሆኑ አሁንም በመኖራቸው ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

70. ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው ያወጡትን ወጪ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት አካተው ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚያቀርቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 65,725,429.61 ከውስጥ ገቢ የተከፈለ፣ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተና ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ተገኝቷል። በተጨማሪም በአንድ መ/ቤት ደግሞ ሪፖርት ማድረግ ከሚገባው መጠን ላይ ብር 4,700,229.17 በማሳነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል።

71. ይህም አሠራር ህጋዊ ካለመሆኑም በላይ የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ እንዲሆን ያደርጋል። በተጨማሪም የመ/ቤቶቹ ትክክለኛው የፋይናንስ አፈጻጸምና ገፅታ እንዳይታወቅ ያደርጋል።

72. ይህንን አስመልክቶ ባለፉት ዓመታት ሪፖርቶቻችን በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (970/2008 እንደተሻሻለው) በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብ

ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ብናሳስብም አንዳንድ መ/ቤቶች አሁንም ከድርጊቱ ሊታረሙ ባለመቻላቸው በገንዘብ ሚኒስቴርም ሆነ በምክር ቤቱ ተገቢው የተጠያቂነት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል።

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

73. በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ88 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,301,454,860.35 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል።

74. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች መካከል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 445,781,634.00፣ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 213,767,213.72፣ መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 125,843,637.00፣ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 107,026,553.84፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ብር 59,896,212.41፣መደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 58,638,207.92 እና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 45,228,032.65 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

75. የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታው ሲተነተን ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 230,432,305.20፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 304,489,394.63፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 232,452,595.52 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 7,968,195.76 ሲሆን ቀሪው ብር 526,112,369.24 የቆይታ ጊዜው የማይታወቅ ነው።

76. በፓራግራፍ 74 ከተጠቀሰው ተከፋይ በተጨማሪ በ9 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 385,575,238.97 ተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ ቢሆንም ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የተከፋይ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።

77. በመሆኑም የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ በፋይናንስ ሕጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፈልና ትክክለኛነቱን ማጣራት ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብም ዝርዝር ማስረጃ በጥንቃቄ ተጣርቶ ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል።

የበጀት አጠቃቀም

ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

78. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ53 መ/ቤቶችና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ተደልድሎ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና በጀት ሳያዛውሩ ከመደበኛ በጀት ብር 312,314,378.22 እና ከካፒታል በጀት ብር 208,375,565.99 እና ከውስጥ ገቢ ብር 10,676,983.96 በድምሩ ብር 531,366,928.17 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

79. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና ሳያዛውሩ ሥራ ላይ ካዋሉት መ/ቤቶች መካከል ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 111,987,647.53፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 79,615,377.18፣ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 76,710,149.04፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 38,598,157.84፣ የወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 35,664,551.36፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 29,063,652.11፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 26,797,772.27 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 23,487,495.67 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

80. በጀት ሳይፈቀድ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተከለከለ በመሆኑ መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተፈቀደላቸውን አሠራር በመከተል በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ ለበርካታ ዓመታት እንዲያርሙ አስተያየት የተሰጣቸው ቢሆንም ጉዳዩ እየተሻሻለ ባለመሆኑ ምክር ቤቱና የገንዘብ ሚኒስቴር ተገቢውን አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የንብረት አስተዳደር

81. በየዓመቱ በምንሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሠረት በርካታ መ/ቤቶች የንብረት አስተዳደራቸውን ለማሻሻል ጥረት እያደረጉ ቢሆንም አሁንም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በገሃድ ይታያሉ፡፡ በዚህ ረገድ በ2010 በጀት

ዓመት ሂሳብ ላይ ኦዲት ሲደረግ ከንብረት አስተዳደር አንፃር የሚከተሉት ጉድለቶች ታይተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	45	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	35	3
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	17	3
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /ስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	19	4
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	35	4
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	62	4
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	80	13
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	36	2
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	24	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው 157 የተለያዩ ተሽከሪካሪዎችና 24 ሞተር ብስክሌቶች ሲሆን በ4ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት ያልተገለጸ	1	11
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸው (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር 2,956,884.52 ይገኙበታል)	28	

የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፣	2	
የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው ዋጋቸው ብር 20,346.01 እና 1 ታብሌት ኮምፒዩተር፣ 18 የላቦራቶሪ ዕቃዎች	2	1
በዱቤ ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ንብረት (ዋጋቸው ብር210,220.76 የሆነ)	1	
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	6	6

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

82. በመሆኑም የየመሥሪያ ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራና በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

83. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ጉድለቶች ታይተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት	
	ተሽከርካሪ	ሞተር ብስክሌት
ሊብሬ ያልቀረበላቸው በ29 መ/ቤቶችና 1 ቅርንጫፍ	174	41
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	373/4	42
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው በ7 መ/ቤቶችና 1 ቅርንጫፍ	11	28/63*
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	300	21
የሻንሲ ቁጥር የሌላቸው	1	
የሞተር ቁጥር የሌላቸው በ2 መ/ቤትና 1 ቅርንጫፍ	31	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	2	1
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው /ጌጅ/ የማይሰራ	11	
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደራጁ	10	11
በኃላፊ ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረገ ተሽከርካሪ	3	
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ በ3 መ/ቤትና 1 ቅርንጫፍ	14	2

መኖራቸው ታውቋል፡፡

84. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው፣ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸውና የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ እንዲሁም ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ

85. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት በየሩብ ዓመቱ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS) እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service - ESPES) ኦዲት የአገልግሎቱ አቅራቢ በሆኑት በወረዳና በክልል ደረጃ በሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክተሮች እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

86. በዚህም መሠረት ከሁሉም ክልሎች በናሙና በተመረጡ በ264 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ ታቅዶ በ231 ወይም 87.5% ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ የማጠቃለያ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለመፈጸም ተችሏል፡፡

87. ለዕቅድ ክንውን ማነስ ዋነኛ መንስኤ የሆነው እጅግ አስቸኳይ የሆኑ ሰፋፊና የተወሳሰቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች በተለያዩ አካላት በመቅረቡ በርካታ የሰው ሀይል ከዚህኛው ኦዲት ሥራ ላይ በማንሳት ልዩ ኦዲቶቹን እንዲያከናውኑ በመደረጉ ነው፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ

88. በገንዘብ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ 2010 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የተጠቃለለ የገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላከ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

89. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ለመሰብሰብ ያቀደውን ገቢ በታቀደው መሰረት የሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት አመቱ ከስድስት የመንግስት የልማት ድርጅቶች

ብር 8,883,717,000 ለመሰብሰብ አቅዶ ብር 4,679,310,831.49 ወይም 52% ብቻ መሰብሰቡ፤

90. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚድሮክ ወርቅ አምራች ድርጅት ከወርቅ ምርት ላይ የመንግሥት ድርሻ ብር 19,538,457.33 ገቢ የሰበሰበ ቢሆንም ያመረተውን ወርቅና ከሽያጭ የተገኘውን መጠን የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ባለመቅረቡ የመንግስት ድርሻ ሊሰበሰብ በሚገባው ልክ ስለመሰብሰቡ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

91. የገንዘብ ሚኒስቴር በ2010 በጀት ዓመት ውስጥ ቀደም ብለው ከተሸጡና በበጀት ዓመቱ ከሚሸጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ ገቢ፣ የሊዝ ክፍያና የብድር ተመላሽ በድምሩ ብር 4,236,900,000.00 ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም የተሰበሰበው ገቢ ብር 2,654,550,000.000 (63%) ብቻ መሆኑ፤

92. መንግስት ከውጭ ሀገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነት ለልማት ድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2010 በጀት ዓመት እስከ ሰኔ 30/2010 ድረስ ከሰባት ድርጅቶች መሰብሰብ የነበረበት ዋና ገንዘብ፤ ወለድና ቅጣት በድምሩ ብር 3,869,987,316.72 ገቢ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

93. በፌዴራል መንግስት የ2010 የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት መግለጫ መሠረት ኦዲት ሲደረግ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4202 ላይ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ላይ የሚፈለግ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 8,169,401.13 መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን በጉድለት ከሚታየው ጥሬ ገንዘብ ውስጥ ብር 7,535,863.54 በ11 መ/ቤቶች ላይ የሚፈለግ ጉድለት ቢሆንም ገንዘቡን ለማስመለስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

94. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ካሉም ሆነ ከተሸጡ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ በመልሶ ማበደር ብድር ከሰጣቸው ድርጅቶችም ዋናውን ገንዘብ፣ ወለድና ቅጣት በዕቅዱ መሠረት ተገቢውን ሥርዓት ዘርግቶ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ የወርቅ ምርት የመንግስት ድርሻንም በተመለከተ የተመረተውንና የተሸጠውን ምርት ጭምር የሚያሳይ በውጭ ኦዲተሮች ተመርምሮ በተረጋገጠ ሂሳብ መሠረት ሊሰበስብ ይገባል፡፡

የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ

95. መ/ቤታችን ከፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲት በተጨማሪ በክዋኔ ኦዲት ላይ ትኩረት ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች እንዲሁም ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ ማሳካታቸውን ለማረጋገጥ በየካቲት 2010 ዓ.ም ተጀምረው እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም የሚጠናቀቁ 24 የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን ታቅዶ ነበር።

96. በዚህም መሠረት የ23 አዳዲስ ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በታቀደው መሠረት ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን የአንዱ ሥራ ደግሞ ተጀምሮ ሥራው ሣይጠናቀቅ ወደ 2011/12 የኦዲት ዘመን ተሸጋግሯል። የክትትል ኦዲቶችን በተመለከተ የ5 የክትትል ኦዲቶች ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቶቹ ወጪ የሆኑ ሲሆን ቀሪውን አንድ የክትትል ኦዲት ግን ማከናወን አልተቻለም። ኦዲቱ ተጀምሮ ሥራው ሳይጠናቀቅ ወደ 2011/12 የኦዲት ካላንደር የተሸገረውን ሣይጨምር የዓመቱ የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ ክንውን አፈፃፀም 93.33% ሆኗል።

97. የኦዲት ሪፖርታቸው ወጪ የሆኑት የ23 አዳዲስና የ5ቱ የክትትል ኦዲት ሪፖርቶች ለምክር ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ስርዓት አፈጻጸም ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

98. የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ድርጅት በማቋቋሚያ ደንቡ ቁጥር 328/2006 መሠረት የኢንዱስትሪውን የግብዓት ችግር ለመቅረፍ የሚያስችሉ ጥናቶችን በማጥናት እና ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎችን (Priority) በማስቀመጥ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት፣ ማስተዳደር እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማስተላለፍ ሲገባው ኦዲቱ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ በዚህ ረገድ የሠራው ሥራ አለመኖሩ፤

99. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በዓይነት፣ በጥራት እና በብዛት በመለየት በእስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅዱ በማካተት የግብዓት ችግሮችን መፍታት ቢኖርበትም ከዓመታዊ ዕቅድ ውጭ የረጅም እና መካከለኛ ጊዜ አቅጣጫ የሚያሳይ የፀደቀ ስትራቴጂክ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፤

100. ድርጅቱ በ2008 በጀት ዓመት ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዘርፍ በብር 270 ሚሊዮን ከአገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ገዝቶ ለማቅረብ ያቀደ ቢሆንም ግኘውን አለመፈፀሙ፤ በተመሳሳይ ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማለትም የተዳመጠ ጥጥ፣ ብትን ጨርቅ፣ አክሰሰሪ፣ ትሪም ቀለም እና ኬሚካሎችን በብር 1.9 ቢሊዮን ገዝቶ ለማቅረብ አቅዶ የተዳመጠ ጥጥ ግዢ ብቻ የፈጸመ ሲሆን ለምግብና መጠጥ ፋርማሲውቲካል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ደግሞ የማሸጊያ ወረቀት ችግር ለመፍታት በብር 313.8 ሚሊዮን የማሸጊያ ወረቀት ግብዓት ግዢ ለመፈጸም አቅዶ ያላከናወነ መሆኑ እንዲሁም በ2009 በጀት አመት የማኑፋክቸሪንግ ግብአቶች ግዢም ሆነ ሽያጭ አፈጻጸም ካቀደው ከ50% በታች ሲሆን በ2010 በጀት ዓመትም 9,199 ቶን የተዳመጠ ጥጥ (1500ቶን ከውጭ) በብር 357.1 ሚሊዮን ለመግዛት አቅዶ አፈጻጸሙ 2,538 ቶን (27.59%) ወይም ብር 95.8 ሚሊዮን (26.83%) ሲሆን የግብዓት አቅርቦቱ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ድርጅቱ የተሰጠውን የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ችግር የመፍታት ተልዕኮ እያሳካ አለመሆኑ፤

101. በሌላ በኩል ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የተለያዩ ግብዓቶችን የሚያቀርብ ሲሆን ኢንዱስትሪዎቹ በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ በቂ ክትትል የማያደርግና በወቅቱ በማይመልሱት ላይ እርምጃ የማይወስድ በመሆኑ ከአይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ብር 106,568,562.19፣ ከባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ ብር 1,220,662.21፣ ከካኖሪያ አፍሪካ ጨርቃ ጨርቅ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 36,100,506.29፣ ከሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ብር 2,395,261.77 ከካቢረ ኢንተርፕራዝ ብር 38,757,536.72፣ ከኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 3,287,936.76፣ ከሆራ ቆዳ ፋብሪካ ብር 23,728,069.66፣ ከሃበሻ ታኒግ ብር 25,411,631.96፣ ከኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ ብር 1,293,859.42፣ ከዴቨ ኢምፔክስ ቆዳ ፋብሪካ ብር 318,330.12፤፣ ከይልማ እሸቱ ቆዳና ሌጦ ንግድ ድርጅት ብር 791,000.00፣ ከዋይ ኤች ኤ የተባለ ድርጅት ብር 22,160,250፣ ከሃይል ኪሮስ ብር 4,180,500.00፣ ከዲ.ኤ.ቪ. ድርጅት ብር 52,337,500.00 በአንድ በኩል የግብዓት ችግር ለመፍታት የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ

እጥረት አለብኝ እያለ በሌላ በኩል ያለውን ገንዘብ በአግባቡ ባለማስተዳደሩ እስከ የካቲት 2011 ዓ.ም ድረስ በድምሩ ብር 318,551,606.92 ከዱቤ ሽያጭ ያልሰበሰበ መሆኑ፤

102. በመሆኑም የኢንዱስትሪዎቹ የግብዓት አቅርቦት ችግር በፍጥነት ካልተፈታ ከፍተኛ ሀብት የፈሰሰባቸው ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነት የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ ተጨማሪ የሥራ ዕድል እንዳይፈጥሩና የውጭ ምንዛሪ በታሰበው መጠን እንዳያስገኙ የሚያደርግ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ችግሩ ሊፈታ ይገባል። በተጨማሪም ለኢንዱስተሪዎቹ በዱቤ ከቀረበው ግብዓት ያልተሰበሰበው ገንዘብ በአፋጣኝ ሊሰበሰብ ይገባል።

የወጪ ንግድ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

103. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነባር የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋትና አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ በመግባት የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ለማሳደግ የሚያስችል የገበያ ጥናት በዕቅዱ መሰረት ካለማከናወኑም በላይ በ2008 በጀት ዓመት በሶስት አገራት በቻይና፣ ሱዳን እና ህንድ የሰሊጥ ኤግዚቢሽኖችና ኮንፈረሶችን ማስተባበርና እንደ አስፈላጊነቱ መሳተፍ በሚል የተያዘው እቅድ ከቻይና በስተቀር ያልፈፀመ መሆኑ፤

104. በተመሳሳይ በ2009 በጀት ዓመት በሰሊጥ የወጪ ምርት ላይ የገበያ ጥናት ማካሄድ እና በሦስት አገራት የገበያ ቅኝት ለማካሄድ የተያዘው ዕቅድ ያልተከናወነ ሲሆን በ2010 በጀት ዓመትም በቻይና እና ህንድ ዓለም አቀፍ የሰሊጥ ኮንፈረንሶች ላይ ሰሊጥ ላኪዎች እንዲሳተፉ በማስተባበር የገበያ ትስስር ለመፍጠር የተያዘው እቅድ ከቻይና በስተቀር ያለመፈፀሙ፤

105. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በአይነትና በመጠን የሚያድግበትን ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በበቂ ሁኔታ ያልዘረጋ ከመሆኑም በላይ ወጪ ምርቶች በመጠን እንዲያድጉና እንዲስፋፉ የሚያደርግ ድጋፍና ክትትል በሚፈለገው ደረጃ እያደረገ አለመሆኑን እንዲሁም የወጪ ንግድ ላይ የሚፈለጉ ምርቶችን ለይቶ በየጊዜው ለላኪው የሚያሳውቅበት እና አብሮ የሚሰራበት ሁኔታ ያለመኖሩን በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከቀረበላቸው ላኪዎች ከሰጡት አስተያየት ለማወቅ ተችሏል።

106. በአጠቃላይ የወጪ ንግድ እንቅስቃሴው ውስን በሆኑና የግብርና ምርቶች ላይ ብቻ በመወሰኑ በአይነት፣ በብዛትና በጥራት ለአለም ገበያ ማቅረብ ባለመቻሉ እንዲሁም የግብርና ምርቶች እሴት ያልተጨመረባቸው፤ ተወዳዳሪ ያለመሆንና የዋጋቸውም መቀዛቀዝ፤ የኤክስፖርት ምርቶች ግብይት እና አቅርቦት ሰንሰለት የተቀላጠፈ አለመሆን እና ወደ ዘመናዊ ግብይት ሥርዓት ያልገቡ ምርቶች የኤክስፖርት ድርሻ በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ ባለመቻሉ የወጪ ንግድ የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በሚፈለገው ደረጃ እንዳያድግ እንቅፋት መሆኑ፤

107. በመሆኑም በ2008 በጀት ዓመት ከግብርና ምርቶች፣ ከማኑፋክቸሪንግ፣ ከማዕድን እና ከሌሎች ዘርፎች ወጪ ምርቶች በድምሩ 4.22 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.86 ቢሊየን (68%)፤ በ2009 በድምሩ 4.75 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.91 ቢሊየን (61%)፤ በ2010 በድምሩ 5.23 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.83 ቢሊየን (54%) ብቻ በመሆኑና በአጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ ግኝቱ ዕድገት የማይታይበትና ባለበት የቆመ ከመሆኑም በላይ ከግብርና ዘርፍ ውጭ ያሉትም እንደ ማኑፋክቸሪንግ፣ ማዕድን እና ሌሎች ዘርፎች እምብዛም ለውጥ የማይታይባቸው በመሆኑ የወጪ ንግዱ ችግሮች በጥናት ተለይተው ሊቀረፉ ይገባል።

108. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ምርቶች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ለማረጋገጥ የሚያስችለው ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ከባለድርሻ አካላት ጋር ሊከታተል የሚገባ ቢሆንም በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው መጠይቅ የቀረበላቸው ላኪዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋጋ አሳንሰውም ሆነ አስበልጠው በሚልኩ ላኪዎች ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ የሚወስድበት ስርአት የሌለ መሆኑን፤ ወቅታዊ የዋጋ ተመን መረጃ የማይልክላቸው መሆኑን፤ የዋጋ ተመን መረጃ የማይደርሳቸው በመሆኑ ተወዳዳሪነታቸውን የሚቀንስባቸው መሆኑንና ወቅታዊ የመላኪያ ዋጋ ባለማወቅ ውል በመግባታቸው የኮንትራት ውል የሚያፈርሱበት ሁኔታ መኖሩን የገለጹ መሆኑ፤

109. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላኪዎች የሚሰጠው የወጪ ንግድ ፈቃድ ለተሰጣቸው አላማ መዋላቸውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ለኤክስፖርት ማበረታቻ ተብሎ ለላኪ ድርጅቶች የሚሰጠውን ብድር ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ክትትል የማያደርግ በመሆኑ ላኪዎች ብድሩን ለገቢ ወይም ሌላ ንግድ የሚጠቀሙበት መሆኑ፤

110. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጪ ንግድ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ላይ ጥናት በማከናወን ሊለይ እና የመፍቻ ስርአት ሊዘረጋ የሚገባ ቢሆንም የወጪ

ንግድ ማነቆዎችን ለመፍታት ጥረቶች ቢኖሩም ግልፅ የሆነ የመፍቻ ሥርዓት ባለመኖሩ፤ የኮንትሮባንድ ኤክስፖርት ንግድ፤ የማኔጅመንትና የቴክኒክ አቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦት ውስንነትና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ችግር የመሳሰሉት ማነቆዎች ከመፍታትና ወጪ ንግዱን ከማቀላጠፍ ይልቅ የመወሳሰብና የመስፋፋት ሁኔታ የሚታይባቸው መሆኑ፤

111. በመሆኑም አሁን ለሚስተዋለው የወጪ ንግድ ችግር ግልፅ የመፍቻ ሥርዓትና ስትራቴጂ በማስቀመጥ የኮንትሮባንድ ንግድ፤ የማኔጅመንትና የቴክኒክ አቅም ውስንነት፣ የግብዓት አቅርቦትና የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ችግሮችን በመፍታት የወጪ ምርትና ንግድ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ አሁን አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ችግር ጭምር ለመፍታት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ ይገባል።

የስሁሉ ኮንትራት አሰጣጥ እና አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

112. የመገናኛ ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የስሁሉ ኮንትራትን በመንግስት እና በግል ሽርክና (Public Private Partnership PPP) አግባብ አገልግሎቱን ለግል ሴክተር ከመቅረቡ በፊት ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው እንደ ባንክ፣ ፖስታ ቤት ወዘተ. በመሳሰሉት የመንግስት መ/ቤቶች አገልገሎቱን ከመስጠት የተሻለ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ስለመሆኑ የተረጋገጠበት ጥናት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ያለመቻሉ፤

113. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስሁሉ አገልገሎት ጨረታውን ካሸነፈው ግሎባል ኮምፒዩቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር ጋር ያደረገው ውል በግዥ ሰነዱ (Request for proposal (RFP)) መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኮንትራት ሰነዱ አንቀጽ 24 ላይ ውሉ ከሰብሲደሪ ወይም አሶሼት ካምፓኒ በስተቀር ለሶስተኛ ወገን እንደማይተላለፍ ተገልፆ እያለ (…any assignment or transfer of USB contract or any rights hereunder by either party shall be prohibited except among the subsidiaries, Associates or Group companies of the partner) ጨረታውን ያሸነፈው ግሎባል ኮምፒዩቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እ.ኤ.አ ሀምሌ 5 ቀን 2011 በቁጥር UBS/0005/2011 በተጻፈ ደብዳቤ የኮንትራት ውሉን ምንም ዓይነት የባለቤትነት ድርሻ ለሌለውና Subsidiary ወይም Associate ላልሆነው ለክፍያ ፋይናንሽያል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር ስራውን አላግባብ ያስተላለፈ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱም አላግባብ የተፈቀደ መሆኑ፣

114. በሌላ በኩል ክፍያ ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የተ/የግ/ማህበር የተቋቋመው የካቲት 2002 ዓ.ም ሲሆን ለአዲስ አበባ አገልግሎት ግንቦት 30 ቀን 2002 የወጣው የጨረታ ሰነድ የሚጠይቀውን የ5 ዓመት የስራ ልምድ እና ቢያንስ በ4 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የሰራ የሚሉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሳለ የተጠየቀውን መስፈርት ሣያሟላ አገልግሎቱን እንዲያቀርብ መደረጉ፤

115. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስሁሉ ኮንትራት (unified billing system (UBS 1)) አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ከግሎባል ኮምፒዩቲንግ ሶሉሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ጋር ዋጋ እና ከዋጋ ጋር ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች የሚያደርገው ድርድር በግዥ ህጉ መሰረት መሆን ሲገባ አሸናፊው ተጫራች ግሎባል ኮምፓቲንግ ሶሉሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ለUBS 1 ያቀረበው ዋጋ ብር 1.43 ሆኖ እያለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከድርጅቱ ጋር ድርድር አደረግሁ በማለት ድርድር የሚደረገው ዋጋ ለማስቀነስ ሆኖ ሳለ ከዚህ በተቃራኒው ቫትን ሳይጨምር ለአንድ ትራንዛክሽን ዋጋውን በብር 1.13 እንዲጨምር በማድረግ በብር 2.56 በመዋዋሉ የስሁሉ አገልግሎት ከተጀመረበት ከየካቲት 2005 ዓ.ም እስከ ህዳር 2011 ዓ.ም ድረስ ሊከፈል የማይገባ ብር 70,173,000.00 (ሰባ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር) አላግባብ እንዲከፈል ማድረጉ፤

116. ግሎባል ኮምፕዩቲንግ ሶሊሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተባለው ድርጅት በገባው ውል መሠረት ከ3 አመት ከ6 ወር በኋላ እ.ኤ.አ ጥር 2015 ስራውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስረከብ ቢኖርበትም ባልተራዘመ ውል ለአንድ አመት ሲሰራ ቆይቶ እ.ኤ.አ ጥር 2016 የውል ማሻሻያ ተደርጎ ኮንትራቱ ለሁለት ተጨማሪ አመት ተራዝሟል። በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በ2017 ጨረታ የወጣ ቢሆንም ሂደቱ ባለመጠናቀቁ እንደገና ውሉ ለአንድ አመት መራዘሙና መጀመሪያ በተገባው ውል መሠረት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ርክክቡ ካለመፈፀሙም በላይ የስሁሉ አገልገሎት ተደራሽነትና ቅልጥፍና ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ ላይ እየደረሰ ያለው ችግር አለመቀረፉ፤

117. በመሆኑም አሁን የሚታየውን ከስሁሉ ክፍያ የአገልግሎት አሰጣጥ፤ ተደራሽነትና ቅልጥፍና እንዲሁም ከውል ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ በህብረተሰቡ ላይ እየደረሰ ያለው

እንግልት በአስቸኳይ መፍትሄ ሊያገኝ ይገባል፡፡

የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

118. የግብርና ሚኒስቴር የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን ለመተግበር የሚያስችለው ደንብ፣ መመሪያ እና ስታንዳርድ ሊያዘጋጅ፤ አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር የሚገባ ቢሆንም የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002 እንዲወጣ ከማድረግ ያለፈ ዝርዝር ጉዳዮችን መሰረት ያደረገ ስራዎችን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያሰራ የሚያስችል ደንብ፣ መመሪያና ስታንዳርድ ያልወጣና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ማድረግ ሲገባው የባለሙያዎች የአቅም ክፍተት፣ የሰው ኃይል እጥረት እና ለዘርፉ ትኩረት ባለመሰጠቱ በሚሉ ምክንያቶች በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተገቢው ሁኔታ እየሰጠ አለመሆኑ፤

120. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማናቸውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ያላቸው እና ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው ስለመሆናቸው ሊያረጋግጥ የሚገባ ቢሆንም በሞጆ ደረቅ ወደብና በቦሌ ካርጎ ኳራንቲን ጣቢያ መግቢያ በሮች በኩል በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚሰጥ ትዕዛዝ መሰረት ከተመረቱ 6 ወር ያለፉቸው እና አስፈላጊውን መስፈርት ያላሟሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማዘጋጃ አክስዮን ማህበር፣ በRaji Agro-industry፣ በሼር ኢትዮጵያ ኃ.የተ.የግል ማህበር፣ በኒዶፒያ ኦርቲ አግሮ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር፣ በመኮቡ ኢንተርፕራዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር፤ በዜድ ኬ ፍላወርስ እና በያሲን ለገሰ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በኒዶፒያ ሆርቲ አግሮ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኩል ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ መፈቀዱን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሠነዶችና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሀላፊዎችና ባለሙያዎች ማረጋገጥ መቻሉ፤

121. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፤ ስርጭት እና አጠቃቀምን በሚመለከት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ስለ ተግባራዊነቱም ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ይህን ችግር ለመከታተልና

ለመቆጣጠር የሚያስችል የተቀናጀ ስርዓት ባለመኖሩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ በኮንትሮባንድ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ስለሚገኙ ህብረተሰቡ እነኚህ ምንጫቸው ያልታወቁ እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከህገ ወጥ ነጋዴዎች ገዝተው በአትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ የሚረጩበት ሁኔታ መኖሩ፤

122. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው መዝግቦ በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ ሰው፣ ዕፅዋት፣ እንስሳት፤ አፈርና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ በማድረግ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት ሊዘረጋ፤ አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር የሚገባ ቢሆንም በተለያዩ ሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለብቻቸው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በማሰባሰብ ለብቻው በተከለለላቸው ቦታ ሰው፣ ዕፅዋት፣ እንስሳት፤ አፈርና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው፤ በየቦታው በተበታተነና ባልተደራጀ መልኩ እንደሚገኙ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገዱበትን ስርዓት አለመዘርጋቱ፤

123. በመሆኑም የፀረ ተባይ ኬሚካል ተመዝግቦና ታውቆ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባበት፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውልበትና የመጠቀሚያ ጊዜው ሲያልፍ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈርና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርስበት ሁኔታ ተይዞ የሚወገድበት ሥርዓት በተገቢው ሁኔታ ተዘርግቶ ካልተተገበረ ሀገራችንን ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል በመሆኑ ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቶ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ወይም ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

124. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/2001 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ላይ ብክለትን ለመከላከል ወይም መጠኑን ለመቀነስ በሚያስችል በማንኛውም ዘዴ መጠቀም ለሚጀምር ለማንኛውም ነባር ድርጅት የሚሰጥ ማበረታቻ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ቢልም አዋጁ ከወጣ ከአስር ዓመት በላይ ቢሆንም ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ደረስ ደንቡ አለመውጣቱ፣

125. በተመሳሳይ ሁኔታ የኢንዱስትሪን ብክለት ለመከላከል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ያላከበሩ ፋብሪካዎች ላይ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 12 መሰረት እርምጃ ለመውሰድ (ለምሳሌ ፋብሪካዎችን ፍቃድ ለመሰረዝ፣ ለማገድና ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር ወዘተ.) መውጣት የሚገባቸው የአፈፃፀም መመሪያዎች ደንቡ ከወጣ ከአስር ዓመት በላይ ቢሆነውም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ደረስ አለመውጣታቸው፤

126. የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ለኢንዱስትሪ የቆሻሻ ዓይነቶች አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አጓጓዝ፣ አመካከን እና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠን እና የአተገባበር ደረጃዎችን ሊያወጣ የሚገባ ቢሆንም እነኚህን ደረጃዎች ባለማውጣታቸው አምራች ድርጅቶች ከፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ (Sedimentation tank) የሚወጣ የፍሳሽ ቅሪት (Sludge Cake) ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሳይሆኑና የሚያስከትለውን ጉዳት ሳያረጋግጡ በተለያየ መንገድ እያስወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤

127. ከፋብሪካዎች የሚወጡ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾችን በተመለከተ አገር አቀፍ ደረጃ ያለ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ፋብሪካዎች በተደረገው ማጣራት አብዛኞቹ ደረጃውን ያልጠበቀ የተበከለ ውሃ ወደ ፍሳሽ መቀበያ እና ወደ ወንዞች የሚለቁ መሆናቸው፤

128. በኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ ቁጥር 159/2001 ብክለትን አስመልክቶ ከማህበረሰቡ የሚመጡ ቅሬታዎች የቀረበለት የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰደውን እርምጃ በ90 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ እንዳለበት የሚገልጽ ቢሆንም ብክለቱ እየቀነሰ ያልመጣ ቢሆንም ማስጠንቀቂያ ከመስጠት በዘለለ ምንም አይነት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑ፤

129. በኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪ ዝቃጭ አወጋገድ ላይ የወጡ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጡበትን የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ ሊያዘጋጁ እና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል መላክ የሚገባቸው ቢሆንም በናሙና ከታዩት 42 ፋብሪካዎች ውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ የዘረጉት 10 (24%) ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት 32 (76%) የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ባለሙያ የሌላቸው ወይም በከፊል ብቻ ያላቸው መሆኑ፤

130. በመሆኑም የኢንዱስትሪ ቆሻሻ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈርና አካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የህግ ማዕቀፉን የተሟላ በማድረግና ተገቢውን ግንዛቤ በመፍጠርና የአወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት መተግበርና ህግና ሥርዓት በማያከብሩት አካላት ላይ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ አሁን እየደረሰ ያለውን ጥፋት በፍጥነት ማስቆም ይገባል፡፡

የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

131. የገንዘብ ሚኒስቴር ኢ.ኤ.አ በ2006 የፕሮጀክት አዘገጃጀት መመሪያ (Project preparation)፣ ኢ.ኤ.አ በ2004 የፕሮጀክት ቅድመ ትግበራ መገምገሚያ መመሪያ (Appraisal guideline for public sector projects) (October 2004) እና ኢ.ኤ.አ በ2008 የፕሮጀክቶች መከታተያና መገምገሚያ መመሪያ (Guidelines for monitoring and evaluation of public sector projects June 2008) ያዘጋጀ ቢሆንም መመሪያዎቹንና ጋይድላይኖቹን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ራሱም የማይጠቀምበት ሲሆን ሌሎች አስፈፃሚ መ/ቤቶችም እንዲጠቀሙበት ክትትል እያደረገ አለመሆኑ፤

132. የመንግሥት ፕሮጀክቶች በተዘጋጀላቸው የጥናት ሰነድ መሠረት ሊጀመሩና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ ቢኖርባቸውም በተለያዩ የፕሮጀክት አስተዳደርና አመራር ችግሮች ምክንያት በክዋኔ ኦዲቱ ከታዩት ፕሮጀክቶች መካከል 75 ፕሮጀክቶች ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት፣ 208 ፕሮጀክቶች ከ1 እስከ 3 ዓመት፤ 54 ፕሮጀክቶች ከ3 እስከ 5 ዓመት እንዲሁም 32 ፕሮጀክቶች ከ 5 ዓመት በላይ ዘግይተው የተጠናቀቁ መሆኑ፤

133. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የመንግስት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመፈቀዱ በፊት የፕሮጀክቶቹ የአዋጭነት ጥናት፣ የቅድመ ግምገማ ሪፖርት (Feasibility, pre-feasibility appraisal) እና ሌሎች የማረጋገጥ ሥራዎችን በአግባቡ ባለመተግበሩ በ290 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ተደጋጋሚ የጊዜ እና የበጀት ክለሣ ተደርጎ ፕሮጀክቶቹ ተፈቅደው ሥራ ሲጀምሩ በነበራቸው ዋጋ ላይ የብር 44,272,740,000.00 ተጨማሪ ወጪ ያስከተሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በቀድሞው የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ስር

የነበሩ 18 ፕሮጀክቶች ትልቁን ድርሻ ብር 32,090,120,000.00 ወይም 72% የሚይዙ መሆኑ፤

134. በሌላ በኩል የአዋጪነት ጥናት ሳይኖራቸው በጀት ተመድቦላቸው የተጀመሩ 16 የመንግስት ፕሮጀክቶች ብር 246,571,379.10 ወጪ ከተደረገባቸው በኋላ የተቋረጡ መሆኑ፤

135. የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ እየተጠናቀቁ ባለመሆኑ ሌላ የልማት ሥራ ሊከናወንበት ይችል የነበረውን እጅግ ግዙፍ ተጨማሪ ገንዘብ እየበሉና አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶች አዋጭነታቸውን ጭምር አጠራጣሪ እያደረገው ከመሆኑም በላይ ተጠናቅቀው ለታለመላቸው ዓላማ ባለመዋላቸውም ከፍተኛ የመልካም አስተዳደር ችግር በመሆን የመንግሥትን ተዓማኒነት እየጎዱ በመሆኑ በፕላንና ልማት ኮሚሽን የተጀመረው የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አመራርና አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ሥራዎች በፍጥነት ተጠናቅቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል።

የ11 አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ስርዓት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

136. በትምህርት ሚኒስቴር የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን የስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍና ወደ ዓመታዊ እቅድ በመመንዘር ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችና ተዛማጅ እቃዎች፣ የተፈጥሮ ሳይንስ የላቦራቶሪ ፈርኒቸር፣ የተፈጥሮ ሳይንስ የስልጠና መስኮች የሚያስፈልጉ የማጣቀሻ መጽሐፍት፣ ዩኒቨርስቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስፈልጓቸውን ኮምፒውተሮችና ተዛማጅ እቃዎች፣ የምግብ ቤት እቃዎች፣ እንዲሁም የጀነሬተር ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ ምንም ዓይነት ግዥ ሳይከናወን ከ67 እስከ 85 ፐርሰንት ግዢ እንደተፈፀመ ተደርጎ ሪፖርት መቅረቡ፤

137. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ግዥዎችን ለመፈፀም በእቃዎች ዓይነት፣ ብዛት እና ጥራት የግዥ ፍላጎቶችን ሊሰበስብ ሲገባ በ2008 እና በ2009 በጀት ዓመታት የአርማታ ብረት እና የሲሚንቶ ግዥ ለማከናወን እቅድ ቢይዝም ስለሚገዛው የሲሚንቶ እና የብረት አይነት (ባለ 6፣ ባለ 8፣ ባለ 10 ወዘተ) እና ብዛት በዝርዝር ያላስቀመጠ ቢሆንም የባለ 10ን ጨምሮ የተለያየ ስፋት ያላቸው 12,440 ቶን የአርማታ ብረት

ግዥ የፈፀመ ቢሆንም በ2008 ከተገዛው ብረት እስከ ጥቅምት 2011 ድረስ ከግንባታ ተርፎ አገልግሎት ላይ ሳይውል የተከማቸ የባለ 10 የአርማታ ብረት በየግንባታ ሳይቱ እያለ በ2011 ዓ.ም በድጋሚ ለግንባታ ከሚያስፈልገው ውጪ በየዩኒቨርስቲው የሚገኙ የግንባታ ቅርንጫፍ ፕሮጀክቶችን የግዥ ፍላጎት ሳይጠይቅ ተጨማሪ ብዛቱና የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ባለ 10 የአርማታ ብረት ግዥ ፈጽሞ ለዩኒቨርስቲዎች ያሰራጨ መሆኑ፤

138. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚገዙ የተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስኮች (ስነ-ሕይወት፣ ፊዚክስ እና ኬሚስትሪ) የትምህርት መሳሪያዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ እና ኮምፒውቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ጋር የብር 2,621,774.00፣ እንዲሁም ለምግብ ቤት እቃዎችና ለተለያዩ ፈርኒቸሮች ስፔስፊኬሽን ዝግጅት፣ የቴክኒካል ሰነድ ግምገማ እና እቃዎቹ ሲቀርቡ በስፔስፊኬሽኑ እና በውል ሰነዱ መሰረት መሆኑን እንዲሁም እቃዎች በተገቢው ሁኔታ ተተክለው ተፈትሸውና አስፈላጊው ስልጠና ለተጠቃሚዎች መሰጠቱን ለማረጋገጥ ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጋር የብር 2,800,000.00 የአማካሪነት ውል የተፈራረመ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዎቹ በውል ስምምነቱ መሰረት እቃዎቹ ገቢ ሲደረጉ በስፔስፊኬሽን መሰረት መሆናቸውን ተገኝተው ያላረጋገጡ በመሆኑ በናሙና በታዩት የእንጂባራ፤ የሰላሌ እና የወራቤ ዩኒቨርስቲዎች በርካታ ግድፈቶች የታዩ መሆኑ፤

139. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለአስራ አንዱ አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚያስፈልጉ የፈርኒቸር፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ ኮምፒውተር እና ተዛማጅ እቃዎች ግዥ በታቀደላቸው ጊዜ ሊፈፅም የሚገባ ቢሆንም ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለአስራ አንዱ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ስራ ለመጀመር የሚያስቻሏቸውን የትምህርት ግብዓቶች በወቅቱ ያላቀረበ በመሆኑ በመማር ማስተማር ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማስከተሉም በላይ ዩኒቨርሲቲዎቹን ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉ፤

140. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለዩኒቨርስቲዎች የምግብ ማዘጋጃ፣ ማብሰያ እና ማቅረቢያ እቃዎችና ጄነሬተር ግዥ ፈጽሞ በጥቅምት 2011 ዓ.ም ወደ አስራ አንዱ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች የላከ ቢሆንም ከዩኒቨርስቲዎቹ ጋር ርክክብ ያልተፈፀመ እና እቃዎቹ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆናቸው፤

141. በመሆኑም የአስራ አንዱ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክት አመራር፤ አስተዳደርና ግብዓት አቅርቦትና ግዥ አፈፃፀም እንዲሁም የግንባታ

ግብዓትና ሌሎች ንብረቶች አያያዝ ቀደም ሲል ከተገነቡት አስራ ሶስቱ እና 1 አስሩ ዩኒቨርሲቲዎች ሁኔታ እምብዛም የማይሻልና ተገቢው ማስተካከያ ያልተደረገበት በመሆኑ አሁንም ትኩረት ተሰጥቶት ማስተካከልና መታረም የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

የእንቦጭ አረም በሀይቆችና ወንዞች ላይ ያስከተለውን ስጋትና ችግር ለመፍታት የተዘረጋውን ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

142. የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት የብዝሃ ህይወት ሀብታችን ከውጪ በሚገቡ ልውጥ ሕያዋን እና ወራሪ መጤ ዝርያዎች እንዳይበከሉና ጥፋት እንዳይደርስባቸው ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርግ በማቋቋሚያ ደንቡ ቁጥር 291/2005 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 19 ሀላፊነት የተሰጠው ቢሆንም እንቦጭ አረምን በተመለከተ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ትኩረት አግኝቶ ብዙ ጥናትና ምርምር እየተደረገበት ያለ በመሆኑ በሚል ማሳበቢያ በህግ የተሰጠውን ሥራ እየሠራ አለመሆኑ፤

143. 1በተመሳሳይ መንገድ የቀድሞ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር የእንቦጭ አረምን ለመከላከልና ለመቀነስ እንዲሁም አረሙ የሚፈጠርበትን ሁኔታ፤ ምንጩን እና የስርጭቱን መጠን በመለየትና በመቆጣጠር ሀይቆቻችንና ወንዞቻችን ጉዳት እንዳይደርስባቸው መጠበቅ ሲገባው ተገቢውን ሥራ ባለመሥራቱ የእንቦጭ አረም ስርጭት በከፍተኛ ፍጥነት ከመጨመሩም ባሻገር በወንዞቻችና ሀይቆቻችን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖና ጉዳት እያስከተለ የሚገኝ መሆኑ፤

144. በኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩትም ሆነ በቀድሞው ውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በኩል የእንቦጭ አረም የስርጭት ሁኔታ፣ በአረሙ የተሸፈነው የውሃ አካል መጠን ምን ያህል እንደሆነ በፌዴራል ደረጃ ጥናት ያልተከናወነ ሲሆን በኦዲቱ ሂደት ከተለያዩ ጥናቶችና ሰነዶች በተገኘው ማስረጃ መሠረት አረሙ ለመጀመሪያ ጊዜ በ2003 ዓ.ም የጣና ሀይቅ ገባር በሆነው በመገጭ ወንዝ ላይ በ3 ሄክታር ላይ ተከስቶ የተገኘ ቢሆንም አረሙን በወቅቱ መቆጣጠር ባለመቻሉ በየጊዜው በተደረጉ ጥናቶች በህዳር ወር 2004 ዓ.ም አረሙ 5 ቀበሌዎችን በማዳረስ 4,000 ሄክታር፣ በ2005 ዓ.ም 15 ቀበሌዎችን በማዳረስ አረሙ 20,000 ሄክታር የሸፈነ ሲሆን ሀምሌ 2006 በተደረገው ደሰሳ በእነዚሁ 15 ቀበሌዎች ወደ 50,000 ሄክታር መስፋፋቱ ታውቋል፡፡

145. በሌላም በኩል በዝዋይ ሀይቅ ዙሪያ ካሉ ወረዳዎች በዱግዳ ወረዳ ባሉ 8 ቀበሌዎች የእንቦጭ አረም የተከሰተ ሲሆን በአጠቃላይ በዝዋይ ሀይቅ ላይ በአረሙ የተሸፈነው የውሃ አካል 40 ሄክታር እንደሚሆን እንዲሁም በእንቦጭ አረም የተሸፈነው የአባያ ሀይቅ የውሃ አካል 1,780 ሄክታር እንደሚደርስ የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን የስራ ሀላፊዎች ገልፀዋል፡፡

146. በኢንስቲዩቱም ሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢው ጥናት ተደርጎ በእንቦጭ አረም የተሸፈነው የሀይቆችና ወንዞች የውሀ አካል መጠን በትክክል ባይታወቅም አረሙ በጣና ሀይቅ፣ በአባ ሳሙኤል ግድብ፣ በቆቃ ግድብ፣ በዝዋይ ሀይቅ፣ በአባያና ጫሞ ሀይቆች እንዲሁም በባሮ፤ በአዋሽና በዓባይ ወንዞች ላይ በመታየቱ በሀይቆቻችንና ወንዞቻችን ላይ የተጋረጠ አደጋ መኖሩን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ እነዚህ ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ አረሙ ያለበትን ሁኔታ ሪፓርት በማዘጋጀት ለመንግስትና ለህዝብ የማያሳውቁ በመሆኑ ጉዳዩ በፌዴራል ደረጃ ትኩረት እንዳያገኝና ተገቢውም እርምጃ እንዳይወሰድ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

147. በአጠቃላይ መጤ አረሙን ለማስወገድ በክልል ደረጃ የሚደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሟላ ጥናት በማድረግ የእንቦጭ አረም የሚፈጠርበትን ሁኔታ፣ ምንጩን እና የስርጭቱን መጠን በማወቅ ለመከላከልና የጉዳት መጠኑን ለመቀነስና ለመቆጣጠር የሚያስችል በጥናት የተደገፈ የተቀናጃ ስትራቴጂ ያልተዘጋጀና ተገቢው ጥረት ያልተደረገ ሲሆን የችግሩ ስፋትና ግዝፈት ግንዛቤ አግኝቶ አስፈላጊው የተቀናጀ ስትራቴጂ ተነድፎና ተገቢው ሀብት ተመድቦለት በአስቸኳይ ካልተተገበረና በፍጥነት ካልተሠራ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ጨምሮ በሀይቆቻችንና ወንዞቻችን ላይ ከፍተኛ ሀገራዊ ጉዳት የሚያደርስ አደጋ በመሆኑ አፋጠኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

148. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ምንነት፣ ለበሽታዎቹ ሊያጋልጡ የሚችሉ መንስኤዎች እና መከላከያ ዘዴዎች በተመለከተ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመደበኛ የትምህርት ካሪኩለም ውስጥ እንዲካተቱ ሊያደርግ የሚገባ ሲሆን ከቅድመ ትምህርት እስከ ሶስተኛ ደረጃ ትምህርት ላሉ ተማሪዎች ተላላፊ ያልሆኑ

በሽታዎች፣ የጉዳት መከላከልና እንክብካቤ ትምህርት ፕሮግራም ፓኬጅ ‘School Health Program for Non-communicable Diseases and Injuries Prevention and Care Service Package’ እ.ኤ.አ በነሐሴ 2017 ያዘጋጀ ቢሆንም ተግባራዊ አለማድረጉ፤

149. የካንሰር ህክምናን ተደራሽ ለማድረግ በጎንደር፣ መቀሌ፣ ሃዋሳ፣ ጅማ፣ ሀሮማያ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች እየተገነቡ ያሉት የካንሰር ህክምና ማዕከላት በተያዘላቸው ጊዜ ግንባታቸው ተጠናቅቆ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ሊሰጡ የሚገባ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ግንባታቸው ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፤

150. በዚህም ምክንያት የካንሰር ህክምና አገልግሎት የሚፈልጉ ታካሚዎች አገልግሎቱን ለማግኘት አዋቂዎች ተኝቶ ለመታከም ከ4 እስከ 5 ወር፣ ለጨረር ህክምና ከ1 አመት ከ3 ወር እስከ 1 አመት ከ6 ወር፣ ኬሞቴራፒ ህክምና ተመላላሽ ለሆኑ 2 ወር አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈጅባቸው ሲሆን ሀኪሞች በትርፍ ሰዓት በሚሰሯቸው ስራዎች ለግል ታካሚዎች ኬሞቴራፒ ቀጠሮ የሌለውና የጨረር ህክምና ቀጠሮ 3 ወር ብቻ የሚፈጅባቸው ከመሆኑም በላይ በግል የጨረር ህክምና ለሚታከሙ ከብር 8000 - 15000 የሚያስፈልጋቸው መሆኑ፤

151. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመሰረታዊ ደረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ሁሉም ጤና ተቋማት ከመሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥበት ሥርዓት ከሚመለከታቸው የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በአገሪቱ ከሚገኙ 290 ሆስፒታሎች እና 3,962 ጤና ጣቢያዎች መካከል 17 በሚሆኑ ሆስፒታሎች እና 43 ጤና ጣቢያዎች ብቻ ዋና ዋና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና እየተሰጠ ሲሆን ወደ ቀሪዎቹ ተቋማት ለማስፋፋት የያዘው ዕቅድ ዘገምተኛ መሆኑ፤

152. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሴቶችን የበለጠ ሊያጠቁ የሚችሉ ተላላፊ ያልሆኑ ካንሰር ነክ በሽታዎች የጡት፣ የማህፀን፣ የማህፀን በር ጫፍ፣ አቫሪ ካንሰር፣ እንዲሁም የደም፣ ታይሮይድ፣ የቆዳና ጉበት በማለት የለየ ቢሆንም የምርመራና የህክምና አገልግሎቱ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለሚገኙ ሴቶች ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ክፍተት የሚታይ መሆኑ፤

153. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን አካል

ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ጎዳና ላይ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከልና መቆጣጠር ስራ ሊሰራ የሚገባ ቢሆንም የአእምሮ ጤና አስመልክቶ ከተወሰኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ከተሰሩት ጅምር ስራዎች በስተቀር ከችግሩ ስፋት አንፃር ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ባደረገ መልኩ የተሰራ ስራ አለመኖሩ፤

154. በመሆኑም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሥርጭትን ለመቀነስ እየተሠራ ያለውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በማጠናከርና በመደበኛ የትምህርት ካሪኩለም ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ እንዲሁም ዋና ዋና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት በሚሰጥባቸው የጤና ተቋማት እንዲሰጥ በማድረግ በተለይ ሴቶችን የበለጠ ሊያጠቁ የሚችሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በመለየት ህክምናውን በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለሚገኙ ሴቶች ተደራሽ በማድረግና ሌሎች ስትራቴጂዎችንም በመንደፍ በፍጥነት እየተስፋፋ የመጣውን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሥርጭት መከላከልና መቆጣጠር ይገባል።

የመንገድና ድልድይ ጥገና አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

155. በየዓመቱ የሚታቀዱት የመንገድ ጥገናዎች በወቅቱ ተጀምረው በተያዘላቸው በጀት፤ ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቁ ለአገልግሎት እንዲበቁ መንገዶች ባለሥልጣን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም ይህን ባለመፈጸሙ ጥገናዎቹ በተያዘላቸው በጀት፣ ጊዜና ጥራት እየተጠናቀቁ አለመሆኑ፤

156. መንገዶችና ድልድዮች ሊያስተናግዱ በሚችሉት የክብደት መጠንና የትራፊክ ፍሰት ልክ እንዲያስተናግዱ በማድረግ ለመንገዶቹና ድልድዮች መደበኛ የጥገና እንክብካቤ ሊደረግላቸው የሚገባ ቢሆንም በየጊዜው የሚያድገውን የትራፊክ ፍሰት እና የጭነት መጠን መነሻ በማድረግ በዓመታዊ ዕቅድ በማካተት መንገዶቹና ድልድዮቹ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ አለመሆኑ፤

157. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ ወይም ለአስቸኳይ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች በራስ ኃይል ፈጣን የሆነ ምላሽ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ቢኖርበትም ይህንን ምላሽ ለመስጠት

የሚያስችል መዋቅር ወይም አደረጃጀት ወይንም የተዘረጋ ሥርዓት የሌለ መሆኑ ታውቋል።

158. በመሆኑም መንገዶችና ድልድዮች ሊያስተናግዱ በሚችሉት የክብደት መጠንና የትራፊክ ፍሰት ልክ ታቅዶ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ወቅታዊና መደበኛ ጥገና የሚያገኙበት፤ ጥገናዎቹም በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ የሚጠናቀቁበት እንዲሁም አስቸኳይ ጥገናዎች የሚከናወኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ ሊፈጸም ይገባል።

የሕንጻ ግንባታና የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት (“የምድብ ‘ሐ’ ሕንፃ”) በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት

159. በቀድሞው የኮንስትራክሽን የመንግስት ሕንጻ ግንባታዎች በህንጻ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት እንደማንኛውም ሕንጻ ግንባታ የፕላን ስምምነት ሊያገኙና የግንባታ ፈቃድ ሂደት ተከትሎ ሊገነቡ የሚገባ ቢሆንም በሕንጻ አዋጁ መሰረት ዲዛይናቸው እንዲጸድቅ የማይደረግ እና የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው እንዲሁም መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጣቸው እና ተገቢው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሳይኖራቸው አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሆኑ፤

160. የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጡ ከተሞች በ“ምድብ ‘ሐ’ ሕንጻ ስር የሚካተቱ የሕንጻ ግንባታዎች ተገንብተው ሲጠናቀቁ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ መስፈርት ማለትም ግንባታው መጠናቀቁ በአማካሪ መሐንዲስ ሳይረጋገጥ፤ ሕንጻው በፕላኑ መሰረት ስለመሰራቱ ቁጥጥሩን ባደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ሣይረጋገጥ፤ የህንጻዎች መግቢያ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆኑ ሣይጣራ፣ የባለመስታወት ግድግዳ ለሚገጠምላቸው ሕንጻዎች ነጸብራቁ በነዋሪው ላይ ችግር አለማስከተሉ ሣይረጋገጥ ፈቃድ የሚሰጥ መሆኑ፤

161. በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና እና በሠነድ ክለሳ ከታዩት ግንባታዎች ውስጥ 51 ህንጻዎች ያለመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው፣ 66 ህንጻዎች መጠቀሚያ ፈቃድ ኖሯቸው ነገር ግን አዋጁ ከሚፈቅደው ውጭ አገልግሎት የሚሠጡ መሆናቸው (ሊፍት ሳይኖራቸው፣ እሳት አደጋ መከላከያ ሳይገጠምላቸው፣ ከተፈቀደው ግንባታ ውጪ ወለል በመጨመር፣ አደጋ በሚያደርስ መልኩ በውስጥና በውጭ የማጠናከርያ ስራዎችን በመስራት አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸው እና 37 ህንጻዎች ለመኪና ማቆምያ ፓርኪንግ የተፈቀደውን ቤዝመንት ለሌላ አገልግሎት ለስቶር፣ ለባንክ ማከራየት፣ በከፊል ለሌላ አገልግሎት፣ ለመጋዘን

አገልግሎት እንዲውል ያደረጉ መሆኑ፤

162. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንባታዎች ከታለመላቸው የአገልግሎት ዘርፍ ውጭ ወደ ሌላ አገልግሎት ለመቀየር ተፈልጎ ጥያቄ ሲቀርብ ከዲዛይን አኳያ ብቁ መሆናቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ያልተገበረ መሆኑ፤

በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አፈጻጸም ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

163. የገንዘብ ሚኒስቴር በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 16 መሠረት የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ እና የሚመለከታቸው አካላት በስራ ላይ እንዲያውሉት ሊያደርግ ሲገባ መመሪያውን ያላወጣ በመሆኑ የየክልሉ ፋይናንስ ቢሮዎችና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የተለያዩና ወጥ ያልሆኑ ውሎች አዘጋጅተው በመዋዋል እና ውሉን እንደ መመሪያ በመጠቀም ስራውን እየሰሩ የሚገኙ መሆኑናቸውን፤

164. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንዱን በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ሊወስን እንደሚገባ በኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 995/2009 አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 2 ላይ የተደነገገ ቢሆንም ይህ ኦዲት ሪፖርት እስከተላከበት ጊዜ ድረስ ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ሣያዘጋጅና ሳይወስን ለወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ከተመደበው ብር 10 ቢልዮን ውስጥ እስከ ጥር 2011 ወደ 9.1 ቢሊዮን ብር ወጪ ሆኖ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ማድረጉ፤

165. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ መሠረት ከባንክ የሚደርሰውን የፈንዱን አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግስት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ ቢኖርበትም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም ባንኩ በአዋጅ ከተገለፀው ውጭ ከወከላቸው ዘጠኙ ክልሎች እና ሁለቱ የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮዎች የፈንዱን አጠቃቀም የሚያሳይ የተመረመረ ሪፖርት የማይደርሰው በመሆኑ በአዋጁ መሠረት የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያቀረበ አለመሆኑ፤

166. የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ የታለመለትን ውጤት እንዲያስገኝ በአዋጁ መሠረት ሀላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም አካላት የተጣለባቸው ግዴታዎች

ሊወጡ ይገባል። በመሆኑም የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድም እንደ ስሙ የሚዘዋወርና የመስሪያ ገንዘብን ደችግር የሚቀርፍና ብዙዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ አንድ ቦታ ተይዞ የሚቀር እንዳይሆን የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ብዛት፤ የተሰጣቸው ብድር መጠን፤ የብድሩ አመመላለስ እና ኢንተርፕራይዞቹ ያሉበት ሁኔታ ማለትም ችግሮቻቸውንና ሊደረግላቸው የሚገባውን ድጋፍ ጭምር የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርትና የተመረመረ ሂሳብ በአስቸኳይ ለሚኒስትሮች ም/ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሊቀርብ ይገባል።

የልዩ ኦዲት ስራዎች

167. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት የተጠየቁ 25 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተጀምረው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 14 ኦዲቶች ሥራቸው ተጠናቀው ሪፖርቱ ለጠያቂው አካል የተላከ በመሆኑ የቀሩት 11 ኦዲቶች በመሠራት ላይ ናቸው። የተጠናቀቁት ኦዲቶች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል።

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

168. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው የሚታወቅ ቢሆንም አብዛኞዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በተባለው ጊዜ ውስጥ እርምጃ መውሰድ ሳይሆን ሊወስዱ ያቀዱትን እንኳ እያሳወቁ አይደለም።

169. የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንደተጠናቀቀ የማስተካከያ መርሃ ግብር እንዲልኩ ከተጠየቁት ኦዲት ተደራጊዎች መካከል ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የማስተካከያ መርሃ ግብሩን የላኩት 48 ብቻ ናቸው። በሌላ በኩል በ2010 ኦዲት ወቅት የ2009 በጀት ዓመት ኦዲትን አስመልክቶ የተወሰደውን እርምጃ ለማጣራት ክትትል ሲደረግ የተለያዩ የኦዲት ግኝት ከተገኘባቸው 148 ኦዲት ተደራጊዎች መካከል የተወሰኑት ብቻ ውሱን እርምጃ የወሰዱ ሲሆኑ በ2009 ኦዲት ወቅት አላግባብ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ በ108 መ/ቤቶች ይመለስ ከተባለው ብር 228,717,664.13 ውስጥ ተመላሽ መደረጉ በክትትል ኦዲት የተረጋገጠው ብር 12,536,323.36 ወይም 5.48% ብቻ ነው። በተጨማሪም ኦዲቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ብር 13,697,724.66 ማስመለሣቸውን ሦስት መ/ቤቶች ያሳወቁን ቢሆንም ለጊዜው በኦዲተሮች አልተረጋገጠም። በሌላ በኩል በ2009 በደንብና መመሪያ መሠረት ባለመሰብሰቡ እንዲሰበሰብ አስተያየት ከተሰጠበት የ2009 ገቢ ግብር ብር 198,199,027.59 ውስጥ መሰብሰቡ የተረጋገጠው ብር 59,966,560.87 ወይም 30.3% ብቻ መሆኑ ታውቋል።

170. ከሌሎች ዓመታት በተለየ ሁኔታ በዚህ ዓመት ም/ቤቱ በተከበሩ አፈ-ጉባኤ የሚመራ ልዩ ኮሚቴ በማቋቋም በኦዲት በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች የማስተካከያ እርምጃ ስለመውሰዳቸው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር አድርጓል። በዚህም የተነሣ በተለይ የከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ እስከ አሁን ለሚታዩት የኦዲት ግኝቶች አንዱ መንስኤ የሆነው ከተመን ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሲሆኑ የተመን መመሪያ ተዘጋጅቶ በዚህ ዓመት የፀደቀ በመሆኑ ከ2011 ኦጋማሽ ጀምሮ ለሚያዙት ሂሳቦች መፍትሔ እንደሚሆን ይታመናል። በተመሳሳይ መልኩ ከመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች አመራርና አስተዳደር ጋር የተያያዙ የኦዲት ግኝቶችን ለመቅረፍ የሚያስችል ሥርዓት በፕላንና ልማት ኮሚሽን በመዘርጋቱ በዚህ ረገድ የሚታዩ ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ሊቃለሉ እንደሚችሉ ይጠበቃል።

171. ነገር ግን አላግባብ ከፍያዎች በመፈጸማቸው ይመለሱ የተባሉ ገንዘቦችን በማስመለስ ረገድ አብዛኛዎቹ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አሁንም አጥጋቢ ውጤት አላስገኙም። በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሰበሰቡ የተባሉ ውዝፍ የገቢ ሂሳቦችን በተመለከተም ከሌሎች ዓመታት የተሻለ እንቅስቃሴ ቢደረግም የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አልመጣም።

172. በዚህ ረገድ በቅርቡ መጋቢት 16 ቀን 2011 የተከበሩ አፈ-ጉባኤ በመሩት መድረክ ኦዲት ተደራጊዎች ከ2002 እስከ 2009 በተደረጉት ኦዲቶች ይመለሱ ተብሎ እስከዚያን ጊዜ ያላስመለሱትን ገንዘብ በተመለከተ በሁለት ወራት ውስጥ ገንዘቡን አስመልሰው ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እንዲያሳውቁ ጥብቅ ማሳሰቢያ ቢሰጡም ድጋሚ የማስተካከያ መርሃ-ግብር ከላኩት 27 መ/ቤቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ መ/ቤቶች ይህ

ሪፖርት ተጠናቅሮ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የወሰዱትን እርምጃ ለመሥሪያ ቤታችን አላሳወቁም፡፡

173. በመሆኑም ከዚህ በላይ መጠበቅ ስለማይገባ፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥና የተጀመሩ ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ የመጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም መድረክ ስምምነት ውጤት ለመጠባበቅ ያዝ ተደርጎ የነበረው ህጋዊ እርምጃ የማስወሰድ እንቅስቃሴ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ጋር በመሆን የሚሠራ ይሆናል፡፡

የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

174. የለውጥ ሥራዎችን በተመለከተ ካለፈው በጀት ዓመት ጀምሮ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ውጤት ተኮር ሥርዓትን ተከትለው ማቀድ ጀምረዋል፡፡ ነገር ግን በመ/ቤትና በሥራ ክፍሎች ደረጃ የተዘጋጁትን ዕቅዶች ቆጥሮ እያንዳንዱ ፈፃሚ ጋር በማድረስ ረገድ የሚንጠባጠቡ ጉዳዮች የሚታዩ በመሆኑ የማጠናከሪያ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል የተሠሩ ሥራዎችን አፈፃፀም በውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት መመዘን የተጀመረ ቢሆንም ተገኘ የሚባለውን ውጤት በየዕለቱ በተፈፀሙ ተግባራት ማስረጃ በማስደገፍ ረገድ አሁንም ቀሪ ሥራዎች ይታያሉ፡፡ በመሆኑም ለብዙ ጊዜ እየተሞከረ ያለውን ነገር ግን በምንፈልገው ፍጥነት ያልሄደውን የአውቶሜሽን ሥርዓት ከጫፍ በማድረስ ይህንን ችግር ለመቅረፍ እየተሠራ ይገኛል፡፡

175. የውስጥም ሆነ የውጭ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍና ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚመለከተውን ወስዶ እየሠራበት ሲሆን አንዳንዶቹ ችግሮች ሙሉ በሙሉ የተወገዱ ቢሆንም ተመልሰው ብቅ እንዳይሉ ከለውጥ ሥራው ጋር በማቀናጀት ዘላቂ አሠራር ተዘርግቶላቸው የመደበኛ ሥራ አካል እየተደረጉ ይገኛል፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

176. በዚህ ረገድ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው

አካል አድርገው እንዲያቅዱና እንዲፈጽሙ ቼክሊስት ተዘጋጅቶ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ በተለይ በፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲት የሴቶች፤ አካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በዕቅድ ውስጥ ተካቶ እየታየ ይገኛል፡፡

177. በሌላ በኩል በመደበኛነት ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት እንደዚሁም የኤ. አይ. ቪ. ኤዲስ ቀናት በተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች እየታጀቡ በመ/ቤቱ እየተከበሩ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በየሁለት ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ አሁንም ቀጥሎ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

178. የነፃ ትምህርት ዕድል በማፈላለግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ለማድረግ ባለፉት ዓመታት እንደተደረገው ሁሉ በዚህም ዓመት 8 ለሚሆኑ ተጨማሪ ሴት ሠራተኞች ዕድሉ የተመቻቸ ቢሆንም አራት ሠራተኞች ብቻ ዕድሉን ተጠቅመው በመማር ላይ ይገኛሉ፡፡

179. የአካባቢ ጉዳዮችን በተመለከተ እየተተገበረ ያለው የወረቀት አልባ ሥርዓት ተጠናክሮ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በሌላም በኩል በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የአካባቢ ኦዲት ተግባራት የተከናወኑ ከመሆኑም በላይ የራሳችንንም ቢሮ አረንጓዴ ለማድረግ ሥራዎች ተጀምረው በመሠራት ላይ ናቸው፡፡

የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ

180. የመ/ቤቱንና የሠራተኛውን አቅም ከመገንባት አንፃር የተለያዩ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

181. እንደሚታወቀው የመ/ቤታችን የማሠልጠኛ ተቋም አንዳንድ ቀሪ ተግባራት ቢኖሩትም ተጠናቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ ዋነኞቹ ቀሪ ሥራዎች ከመዋቅርና የሰው ሀይል ምደባና ቅጥር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነኚህ በሂደት የሚጠናቀቁ ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቀደም ሲል የተዘጋጁትን ሞጁሎች በመጠቀም የሠራተኞቻችንን ክህሎት ለማሳደግ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በተለያየ ዙር ወደ 296 የሚሆኑ ሠራተኞችን በማዕከሉ ለማሠልጠን ተችሏል፡፡

182. ሁሉንም የመ/ቤቱ ሥራዎቻችን በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ ታልሞ ከብሪታኒያ መንግሥት (DFID) በተገኘ የ2,000,000.00 የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ ከሀምሌ 2009 ጀምሮ ሲሠራ የነበረው የዳታ ማዕከል ግንባታ ተጠናቅቆ ሥራ ጀምሯል፡፡ በተጨማሪም ከመንግሥት በተመደበ ብር 10,970,523.72 የአዲሱ ህንፃ ግንባታ አካል ሆኖ በመንግሥት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በኩል ሲከናወን የነበረው የኔትወርክና ተጓዳኝ ሥራ ቢዘገይም በአሁኑ ወቅት ተጠናቅቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሁለቱም ፕሮጀክቶች ሁሉንም የመ/ቤታችንን ሥራዎች በቴክኖሎጂ ለማስደገፍ ያለምነውን ዓላማ በማሳካት ረገድ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ከመሆኑም በላይ ወጪ በመቀነስ፣ የሥራ ጥራት፤ ቅልጥፍናና ውጤታማነትን በማጎልበት ተልዕኳችን በተሻለ ደረጃ እንዲሳካ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

183. ዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሠራ የነበረው የኦዲት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት የአማካሪ ድርጅት ቅጥር ሥራ ረዥም ጊዜ የወሰደ ቢሆንም በቅርቡ የግዥው ሂደት ተጠናቅቆ በአማካሪ ድርጅቱና በገንዘብ ሚኒስቴር መካከል በሚያዝያ 2011 ውል የተፈረመ ሲሆን በያዝነው ግንቦት ወር ሥራውን ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ሲቀረፅ የአራት ዓመት ዕድሜ እንደሚኖረው ታስቦ ቢሆንም አሁን የቀረው አንድ ዓመት ብቻ በመሆኑ የታሰበውን ያክል ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ባይታሰብም የምንችለውን ያህል ለመጠቀም ጥረት የምናደርግ ይሆናል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

184. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 645 እና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 314 በድምሩ 959 ሠራተኛ ነው፡፡ የኦዲት ሥራው በየካቲት ወር 2010 ሲጀመር 423 ኦዲተሮችና 214 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 637 ሠራተኛ በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ 87 ኦዲተሮችና 18 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 105 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን በዚሁ ዓመት ውስጥ 12 (ከድጋፍ 2 እና ከኦዲት 10) ሠራተኞች በጡረታ፣ 1 በሞት፣ 1 በዲሲፕሊን፤ 50 ኦዲተሮችና 22 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 72 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ በአጠቃላይ ደግሞ 86 ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

185. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 451 የኦዲት ባለሙያዎች

(296 ወንዶችና 155 ሴቶች)፣ 206 የድጋፍ ሰጪ (92 ወንዶችና 114 ሴቶች) ሠራተኞች በአጠቃላይ 657 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን 305 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግበው ይገኛል፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት በየወቅቱ ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም ባለው የሠራተኛ ፍልሰት ምክንያት ችግሩን ማስወገድ አልተቻለም፡፡

የ2010 በጀት ዓመትና 2011 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

186. በ2010 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ ብር 124,242,770.86 በጀት ተፈቅዶ የነበረ ቢሆንም በተደጋጋሚ ወጥቶ ባልተሳካው ጨረታ ምክንያት ከሚያዝያ 30 ቀን 2010 ዓ.ም በፊት ብር 47,170,312.25 ገንዘብ ሚኒስቴር ለሌሎች መ/ቤቶች እንዲያስተላልፍ ተደርጎ ከቀረው ብር 87,072,458.61 ውስጥ ብር 79,566,825.75 ወይም 91% ሥራ ላይ የዋለና ያልተሰራበት ብር 7,505,632.86 (9%) የነበረ ሲሆን ለ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው መደበኛ ብር 84,464,860.00 ለካፒታል ብር 17,000,000.00 በድምሩ ብር 101,464,860.00 ውስጥ እስከ መጋቢት 30/2011 ሥራ ላይ ለማዋል የታቀደው የዘጠኝ ወር በጀት ብር 64,537,446.59 ሲሆን በዘጠኝ ወር ውስጥ ስራ ላይ የዋለው ደግሞ ብር 58,080,831.23 ወይም 89.99% ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

187. በኦዲት ተደራጊዎች በኩል አሁንም ያልተሻሻሉና በጊዜ አጠቃቀማችን ላይ ጭምር ተፅዕኖ እያስከተሉ ያሉ ጉዳዮች በኦዲተሮቻችን የሚጠየቁትን ማስረጃዎች በወቅቱ ያለማቅረብ ወይም ያለመስጠት፣ ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት፤ የመውጫ ስብሰባ ከተደረገና ለኦዲተሮች ሌላ ስምሪት ከተሰጠ በኋላ በኦዲት ወቅት ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡትን ማስረጃዎች አሉን በማለት በርካታ ሠነዶችን መ/ቤታችን ድረስ ጭነው ማምጣትና ለረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች አንዳንዴ ሆን ተብሎ እየተፈጠሩ ኦዲተሮቻችንን ጫና ውስጥ በመክተት በተለይ በኦዲት ማጠናቀቂያ ወቅት ትኩረት እንዲያጡና ተገቢውን ጊዜ ሰጥተው ሠነዶቹን እንዳይመረምሩ ጭምር የሚሠሩ ሥራዎች በመሆናቸው ህጉ

የሚፈቅደውን አግባብ ተከትለን እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት በየዓመቱ ተመሳሳይ ችግር የሚፈጥሩ ኦዲት ተደራጊዎች ህግና ሥርዓት ተጠብቆ ሠነዶችና መዝገቦች ኦዲተሮች በጠየቁበት ጊዜ በወቅቱ ሊያቀርቡላቸው ይገባል፡፡

188. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን፤ የመከላከያ፤ የገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፎችንና ሌሎች ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ የፌዴራል መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ኦዲተሮቻችን ከሌላው የመንግሥት ሠራተኛ በተለየ ሁኔታ ዓመቱን በሙሉ የሚቆዩት መስክ ላይ ነው፡፡ አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለመስክ የሚከፈላቸው የቀን ውሎ አበል ወጪያቸውን ሊሸፍን ባለመቻሉ ኦዲተሮቻችን አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሥራቸውን በማከናወን ላይ ናቸው፡፡ ለሁለትና ሦስት ቀናት ብቻ መስክ ቢሄዱ ችግሩን እንደምንም ሊቋቋሙ ይችላሉ ተብሎ ሊታስብ ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ዓመቱን ሙሉ የመስክ ሥራ ላይ ስለሚቆዩ ችግሩ እጅግ ግዙፍ ነው፡፡ መንግሥት ይህንን ልዩ የሆነውን ሁኔታ ተገንዝቦ ለችግሩ መፍትሄ እንዲሰጠን ብንጠይቅም እስከ አሁን ያልተፈታ በመሆኑ ምክር ቤቱ ይህንን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶት እንዲፈታልን በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

189. ሌላው በዚህ ዓመት ያጋጠመን ችግር በወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ ኦዲተሮቻችን ሥራዎቻቸውን በአቀድነው ጊዜ ሠርተው ማጠናቀቅ አለመቻላቸው ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ቢሆን ከእኛ ቁጥጥር ውጭ በሆነው ምክንያት ኦዲት ልናደርጋቸው ካልቻልናቸው ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች በስተቀር ጊዜውን ገፋ ብናደርግም ሠራተኞቻችን ባሳዩት ከፍተኛ ቁርጠኝነት የዓመቱን ዕቅድ ማሳካት ተችሏል፡፡ በርግጥም አንዳንዶቹ የሚቀምሱትና የሚጠጡት ነገር ሣይኖራቸው በከባድ ሁኔታ ውስጥም ሆነው ሀላፊነታቸውን በመወጣታቸው በምክር ቤቱ ፊት ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

የ2011/2012 ኦዲት ዓመት ዕቅድ

190. በ2011 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 174 የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ ቀደም እንዳሉት ዓመታት 9 የሚሆኑት ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 165 ተቋማት በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በሌላ በኩል ከመጋቢት 2010 እስከ ጥር 2011

ድረስ 24 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 6 የክትትል ኦዲቶችን በማከናወን 30 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በ273 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡ በሌላም በኩል የመንግሥት የተጠቃለለ ሂሳብ እንዲሁም አሁን እየተሠሩ ያሉ 11 ልዩ ኦዲቶችን ሠርቶ ለማጠናቀቅ ታስቧል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

191. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የእርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት አስደርጎ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊ የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

192. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2010 እና ሪፖርቱን ወቅታዊ ለማድረግ እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም በተከናወኑና ለመ/ቤታችን የደረሱ ኦዲቶች ላይ የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረቡ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

193. በሌላም በኩል መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ሂሣባቸውን ዘግተው በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ 48 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የተሰጠ ኦዲት አስተያየት

194. በ2010 በጀት ዓመት እና ሪፖርቱን ወቅታዊ ለማድረግ ከየካቲት1/2010 እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም ሪፖርታቸውን ያቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 65 ሲሆኑ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች

ሂሳብ ኦዲት 170 በድምሩ 235 ናቸው፡፡

195. በእነዚህ ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) 155፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) 43፣ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 30፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቃውሞ አስተያየት የቀረበባቸው (Adverse) 1፤ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 5፤ ልዩ ኦዲት 1 በድምሩ 235 ናቸው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን

196. ኮርፖሬሽኑ በ2010 በጀት ዓመት መጀመሪያ በነበረው 136 (90 ኦዲተሮችና 46 ድጋፍ ሰጪ) የሰው ኃይል፣ 244 ኦዲቶችን ለማከናወን አቅዶ 232 ኦዲቶችን (88%) የፈጸመ ሲሆን በሌላ በኩል በቁጥር 28 የሚሆኑ ረቂቅ ኦዲት ሪፖርቶች ለደንበኞች ተልከው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምላሽ ያልተሰጠባቸው በመሆኑ ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ ማሳካት አልተቻለም፡፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ አንቅስቃሴ

197. ኮርፖሬሽኑ በ2010 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 38,938,847.00 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 35,831,029.00 ገቢ ያገኘ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ብር 31,737,765.00 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 28,566,900.00 ወጪ ያደረገ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ብር 5,084,890.00 የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

198. የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው የፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ ከሁለት ዩኒቨርሲቲዎች (አንዱ በወቅታዊ የፀጥታ ችግርና ሌላኛው ሂሳቡን ሊዘጋ ባለመቻሉ) በስተቀር በሌሎች የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት በታቀደው መሠረት ተከናውኗል፡፡ ነገር ግን ከመ/ቤታችን ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት የሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች ሂሳብ ኦዲት ስላልተጠናቀቀ የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ ክንውን መቶ በመቶ መፈፀም አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሽፋኑ ካለፉት ዓመታት ወደ ኋላ ተንሸራትቶ 98.87% ሆኗል፡፡

199. በሌላ በኩል የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ 24 አዳዲስና 6 የክትትል ኦዲት በድምሩ 30 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 23 አዳዲስና 5 የክትትል በድምሩ 28 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርገዋል፡፡ በዚህም መሠረት የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም በአንድ የክትትል ኦዲት አንሶ የተፈጸመ ቢሆንም የዕቅድ አፈፃፀሙ አምና ከነበረበት 92.86% ወደ 93.33% ተሻሽሎ ተገኝቷል፡፡

200. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ264 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱን ለማከናወን ታቅዶ በ231 (87.5%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲት ዕቅድ ክንውን በዚህ ደረጃ እንዲያንስ የሆነበት ምክንያት በርካታ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች ከተለያዩ አካላት በመቅረባቸውና የሰው ሃይሉን ለነዚህ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሥራዎች አዛውሮ እንዲሠራ በመደረጉ ነው፡፡ ከመደበኛው ኦዲቶች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በርካታ ልዩ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን ከፊሎቹ ተጠናቅቀው ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን ቀሪዎቹ አሁንም በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

201. በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤት መሠረት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ባለፉት ዓመታት የታዩትን የአሠራር ግድፈቶች በማረምና የተዘረጋውን የመንግሥት የፋይናንስ፣ ግዢ እንዲሁም የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ተከትለው በመሥራት ረገድ አሁንም አብዛኛዎቹ በሚጠበቀው ልክ ለውጥ እያሳዩ አይደለም፡፡

202. ስለሆነም እነዚህ የኦዲት ግኝቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው እርምጃ ተወስዶ ሊስተካከሉና ሊታረሙ ይገባል፡፡ ይህንን ያላደረጉ ተቋማት ደግሞ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተጠያቂ መደረግ አለባቸው፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱና አጠቃላይ ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ28 ጥራዝ፣ አስተያየት ሊሰጥባቸው ያልተቻለ የ11 መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርትና ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው የ49 መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች ለየብቻ ተዘጋጅተው ለተከበሩ አፈ-ጉባዔ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን በምክር ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ በሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተውና ተመርምረው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትልና ግፊት ሊደረግ ይገባል፡፡

203. እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በ2010 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲትም ወቅት በዋነኛነት የኦዲት ግኝት ሆነው የቀጠሉት ከጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ የውዝፍ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ ወይም አለመወራረድ፤ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚከናወኑ ግዥዎችና እንደዚሁም ከህግና ከተዘረጋው ሥርዓት ውጪ አላግባብ የሚፈጸሙ የጥቅማ ጥቅምና ሌሎች ክፍያዎች፤ አላግባብ በብልጫ የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤ ከውል አስተዳደር ጋር የሚታዩ ግድፈቶች፤ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ተደጋጋሚ ግድፈቶች፤ ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፤ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ጉድለቶች፣ ከበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚታዩ ክፍተቶች እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረጉት የክዋኔ ኦዲቶች በርካታ ሊዘረጉ ሲገቡ ያልተዘረጉ ለየመ/ቤቶቹ ቅልጥፍናና ውጤታማነት እንዲሁም ለተልኮ ስኬት አስተዋፅኦ ያደርጉ የነበሩ የህግ እና የአሠራር ሥርዓቶች ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ከተልዕኮ ስኬት አንፃር በርካታ የአፈፃፀም ጉድለቶች ታይተዋል፡፡

204. በመ/ቤታችን የሚደረጉ የፋይናንስና ህጋዊነት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ጉድለቶችንና ክፍተቶችን ብቻ የሚናገሩ ሳይሆን የማሻሻያ አስተያየቶች ጭምር የሚያካትቱ በመሆኑ በአግባቡ ቢተገበሩ የኦዲት ተደራጊዎችን አሠራርና አፈፃፀም በማሻሻል ለተልዕኳቸው ስኬት ዓይነተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር፡፡ በመሆኑም ኦዲት ተደራጊዎች

የሚሰጡት የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቅሙት ራሳቸውን እንደሆነ ተገንዝበውና አምነው ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

205. እስካሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊዎች በዚህ መልኩ አምነው ተገቢውንና በቂ እርምጃ እየወሰዱ ባለመታየቱ ሊስተካከሉና ሊታረሙ ይችሉ የነበሩ የኦዲት ግኝቶች በየዓመቱ ተደጋግመው እየታዩ በመሆኑ በየደረጃው ያሉ አካላት ማለትም የተከበረው ምክር ቤት፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲሁም መ/ቤቶቹ ተጠሪ የሆኑባቸው ተቋማትና የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አግባብ የሆነውን የተጠያቂነት እርምጃ እንዲወስዱ እያሳሰብኩ በጥሞና ስላደመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አባሪ 1

በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እና ባለፉት ተከታታይ ሁለት ኦዲቶች

ሀ/	ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው	X
ለ/	አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	XX

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	2010	2009	2008
		ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት			
1	1	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	XX	XX	XX
		የፋይናንስና ኮሚዩኒኬሽን መ/ቤቶች			
2	1	የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ	XX		
3	2	የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	XX		
4	3	የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን	XX		
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች			
5	1	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	XX	X	X
6	2	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	XX	XX	XX
7	3	ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	XX	XX	XX
8	4	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	XX		
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
9	1	የመገናኛና ኢን/ቴክ ሚኒስቴር	XX		
10	2	የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	XX	X	X
		ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች			
1	1	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የማጠቃለያ ሂሳብ	X	X	X
		የፋይናንስና ኮሚዩኒኬሽን መ/ቤቶች			
2	1	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	X		
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች			
3	1	የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር	X	X	X

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	2010	2009	2008
4	2	የቀድሞው የማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር	X		
5	3	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	X	X	X
6	4	የቀድሞው የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር	X		
7	5	የቀድሞው የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	X		
8	6	የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ	X		
		የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት			
9	1	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
10	2	ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
11	3	ድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
12	4	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
13	5	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
14	6	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
15	7	ትምህርት ሚኒስቴር	X	X	X
16	8	ደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ	X		
17	9	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
18	10	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	X		
19	11	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
20	12	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
21	13	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
22	14	ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
23	15	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
24	1	የአዳማ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
25	2	የወራቤ ዩኒቨርሲቲ	X		
26	3	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	X	X	X

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	2010	2009	2008
27	4	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	X		
28	5	የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ	X	X	X
29	6	የመቱ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
30	7	የፌ/የቴክ/ሙ/ትም/ሥ ኢንስቲትዩት	X	X	XX
31	8	የፌ/የቴክ/ሙያ ት/ሥ/ ኤጀንሲ	X		
32	9	የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
33	10	የኢት/ጨ/ጨ/ኢ/ል ኢንስቲትዩት	X		
34	11	የአ/አበባ ሳይ/ቴክ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
35	12	የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር	X		
36	13	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
37	14	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	X		
38	15	የብሔ/የቆላ/ዝ/ገ/በሽታ መቆ/ማጥፊያ ኢንስቲትዩት	X		
39	16	የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	X		
40	17	የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	X	X	X
41	18	ወልድያ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	X		
42	1	የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	X		
43	2	ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	X		
44	3	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	X	X	X
45	4	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	X		
46	5	የንግድ ሚኒስቴር	X	X	
47	6	የፌዴራል አርብቶአደሮችና ልማት ሚኒስቴር	X	XX	X
48	7	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ም/ቤት	X		
49	8	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	X	X	X

አባሪ 2

ሂሣባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች

ተ.ቁ	የልማት ድርጅቱ ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት	ወደኋላ የቀረበት ዓመት	በቅርቡ ያለበት ሁኔታ (ከታወቀ)
1	ስኮር ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2004	6	የ2005 በጀት ዓመት በኦዲት ስራ ላይ
2	ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር	ሰኔ 30/2005	5	
3	የብረታ ብረትና ኢኒጂነሪንግ ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2005	5	ከ2006 እስከ 2009 በጀት ዓመት በኦዲት ስራ ላይ
4	የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት	ሰኔ 30/2005	5	
5	የኢትዮጵያ እምነበረድ ማምረቻ	ሰኔ 30/2006	4	
6	የትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ኢ.ማ	ሰኔ 30/2006	4	
7	የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት	ሰኔ 30/2007	3	የ2008 በጀት ዓመት በኦዲት ስራ ላይ
8	የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን	ሰኔ 30/2007	3	
9	የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2007	3	
10	የግብርና ምርቶች ምርምርና አቅርቦት ድርጅት	ሰኔ 30/2007	3	
11	አዶላ የወርቅ ማዕድን ልማት ኢ.ማ	ሰኔ 30/2007	3	
12	የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ድርጅት	ሰኔ 30/2007	3	
13	ኢትዮ-ቴሌኮም	ሰኔ 30/2008	3	የ2009 በኦዲት ስራ ላይ
14	የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት ኢ.ማ	ታህሳስ 30/2007	3	
15	የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን	2008	3	ሰኔ 2008 በኦዲት ስራ ላይ

ተ.ቁ	የልማት ድርጅቱ ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት	ወደኋላ የቀረበት ዓመት	በቅርቡ ያለበት ሁኔታ (ከታወቀ)
16	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ስራ ላይ
17	የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት	ሰኔ 30/2008	2	
18	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ስራ ላይ
19	የግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ሪፖርት ዝግጅት ላይ
20	የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ሪፖርት ዝግጅት ላይ
21	የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ሪፖርት ዝግጅት ላይ
22	የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ስራ ላይ
23	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	ሰኔ 30/2009	1	
24	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2008	2	የ2009 በኦዲት ስራ ላይ
25	የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30/2009	1	የ2010 በኦዲት ሪፖርት ዝግጅት ላይ
26	ባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ	ሰኔ 30/2008	2	
27	የመንግስት ሰራተኞ ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ	ሰኔ 30/2009	1	የ20010 በኦዲት ስራ ላይ
28	የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት	ሰኔ 30/2009	1	
29	ሸበሌ ትራንስፖርት አ.ማ	ሰኔ 30 /2009	1	
30	የመንግስት ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት	ሰኔ 30 /2009	1	የ20010 በኦዲት ስራ ላይ
31	የኢትዮጵያ አየር መንገድ	ሰኔ 30 /2009	1	የ20010 በኦዲት ስራ ላይ
32	የኢትዮጵያ ባቡር ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30 /2009	1	የ20010 በኦዲት ስራ ላይ
33	የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	1	

ተ.ቁ	የልማት ድርጅቱ ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት	ወደኋላ የቀረበት ዓመት	በቅርቡ ያለበት ሁኔታ (ከታወቀ)
34	የህንጸ መሳሪያዎች አቅራብ ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	1	
35	የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት	ሰኔ 30 /2009	1	
36	የኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	1	
37	የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ.ማ	ሰኔ 30 /2009	1	የ2010 በኦዲት ሪፖርት ዝግጅት ላይ
38	የኢትዮጵያ መብራት አገልግሎት	ሰኔ 30 /2009	1	
39	የኢትዮጵያ መብራት ኃይል	ሰኔ 30 /2009	1	
40	የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን	ሰኔ 30 /2009	1	የ2010 በኦዲት ሪፖርት ዝግጅት ላይ
41	ግዮን ሆቴሎች ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	1	
42	የኢንዱስትሪ ፐሮጀክቶች አገልግሎት	ሰኔ 30 /2009	1	
43	የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	1	
44	የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት	ሰኔ 30 /2009	1	
45	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30 /2009	1	
46	ኬሚካል እንዱስትሪ ኮርፖሬሽን	ሰኔ 30 /2009	1	
47	የመከላከያ ኮንስትራክሽን ድረጅት	ሰኔ 30 /2009	1	
48	የኢትዮጵያ ልማት ባንክ	ሰኔ 30 /2009	1	

አባሪ 3

ልዩ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶችና የኦዲት አርዕስቶች

ተ.ቁ	የመ/ቤት ስም	የልዩ ኦዲቱ አርዕስት/ ጉዳይ
1	የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ	የሳይበር ታለንት ማነጅሜንት ፕሮግራም
2	አዲስ ቪው ጀንራል ሰርቪስ ኃ/የተ.የግል ማህበር	2001-2009 ዓመታት ከግብር አከፋፈል ጋር የተያያዘ
3	በገንዘብ ሚኒስቴር	የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት፤
4	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	አለም አቀፍ የስንዴ ግዥን የጨረታ ሂደት በተመለከተ
5		የታብሌት ግዥን በተመለከተ
6		የHP Computer ግዥን በተመለከተ
7	የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን	የህዳሴ ግድብ የደን ምንጣሮ የአገልግሎት ግዥ በተመለከተ
8		የ114 የመኪና ግዥን የግዥ ሂደት በተመለከተ
9	የጂኦሲንቴቲክስ ኢንዱስትሪያል ወርክስ ኃ.የተ.የግል ማህበር-	ከጎልደን ትሬዲንግ ጋር የተደረጉ ግዥዎች ፤ የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትለው ስለመፈጸማቸው፤
10	የወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል	ሀዋሳ በቆሎ ምርምር መለስተኛ ማዕከል የግንባታና ቢሮ ዕድሳት፣
11	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት	የባቱ ዲስትሪክት አገልግሎት መስጫ ማዕከል የአንድ ገንዘብ ያዥ ሂሳብ
12	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	ከዕዳት አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ
13	አንበሳ ባንክ፣ በፍ/ቤት ትዕዛዝ	የአዳማ ልዩ ዞን ከ/ፍርድ ቤት ጠያቂነት በአንበሳ ባንክና በአንድ ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብን ጉድለትን በተመለከተ
14	ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	በጅዳ ሳዑዲ አረቢያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ፅ/ቤትና በኢትዮጵያዊያን ኮሚኒቲ ማህበራት መካከል ከገንዘብ አስተዳደርና አያያዝ ጋር በተመለከተ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ቀድሞ ይገኝ ከነበረበት ፒያሳ አካባቢ በመልቀቅ ፍላሚንጎ አካባቢ ወደሚገኘው አዲሱ የመ/ቤቱ ህንጻ ከሰኔ ወር ኢጋማሽ 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተዛውሯል።



የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
ስልክ ቁጥር፡ +251115575701 ድረ-ገጽ www.ofag.gov.et
ኢ-ሜይል- ofagit@ethionet.et ፖ.ሳ.ቁ- 457
f - Office of the Federal Auditor General, Ethiopia